

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
በ ቅ ዱ ስ መ ካ ን
(ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም)
ያ ላ ት መ ብ ት

የሰነድ ማስረጃዎች ።።

በ ብ ፁ ዕ አ ቡ ነ ፊ ል ጶ ስ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን
ትጋት የተዘጋጀና የታተመ ።

እ. ኤ. አ. ጥቅምት ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.
እ. ኤ. አ. ጥቅምት ፲፱፻፺፰ ዓ. ም.

በኢየሩሳሌም ዳኛና ጠበቃ በነበሩት በጀሚል አይ. ሐቢቢ
ከዓረብኛ ወደ እንግሊዝኛ ተተረጐመ ።

በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት በአቶ ገብረሚካኤል ኪዳኔ
ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተረጐመ ።



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።



ግርማዊት እቴጌ መነን እንተ ይእቲ ወለተ ጊዮርጊስ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።



አባ ፊልጶስ ጳጳስ ዘገዳማተ ኢትዮጵያ
እለ በኢየሩሳሌም ።

መ ቅ ድ ም ።

ሰው አንድ መጽሐፍ ወይም ታሪክ በሚጽፍበት ጊዜ ከጻፈው መጽሐፍ በመጀመሪያው ገጽ፣ የሐሳቡን መነሻና መድረሻ የሚገልጽ፣ እንደዚሁም መጽሐፉን ለምን ጉዳይ ይጠቅማል ብሎ የጀመረው መሆኑን የሚያስረዳ መቅድም ወይም የሐሳብ መግለጫ መጻፍ ይገባዋል። ስለዚህ የግል ጥቅም ወይም ከንቱ ውዳሴ በመሻት ሳይሆን፣ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ጥልቅ አስተዋይነትና ክርስቲያናዊ መሪነት፣ በብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ እቡነ ባስልዮስ መንፈሳዊ ቅብዓት፣ በሃገር ቅድስት በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ገዳማተ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ከኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተመርጬ ወደ ኢየሩሳሌም ለጳጳስነት ተግባር በተላክሁ ጊዜ፣ በኢየሩሳሌም በቅዱሳት መካናት በሚገኙት በክርስቲያን ማኅበሮች መካከል የተፈጠረው ስስትና አለመግባባት ባስገኘው የርስ በርስ መጣላትና መነጣጠቅ ተግባር፣ በተለየም ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊው ተግባርዋ ይጠቅሙኛል ብላ የምታምንባቸው የኮፕት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የወዳጅ ጠላት ሆነው፣ በኢትዮጵያውያን ማኅበሮች ላይ በቅዱሳት መካናት ባሉት ገዳሞቻቸውና በንብረታቸው ሁሉ የሠሩትን ግፍና እስከዛሬም ድረስ የሚሠሩትን የጠላትነትና የቅሚያ ሥራቸውን መከላከል ተገቢ በመሆኑና የመልእክቴም ኃላፊነት ስለሚያስገድደኝ ከጥንት ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያን የሰበሰቧቸውን ጽሑፎችና እንዳንድ የቅርብ ተመልካቾች የውጭ አገር ሰዎች የጻፏቸውን ታሪኮች በተቻለ መጠን አጠራቅመን አለአገባብ በግፍ የተወሰደብንን የርስት መብት በሕግ መሠረት እንዲለቀቅልን በመጠየቅ በዘመናችን ላሉት ለጆርዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች ያቀረብነውን የጽሑፍ ማስረጃና አባሪ ማመልከቻ ኢትዮጵያዊና ግፍን የማይወድ እውነተኛ ፈራጅ ሕሊና ያለው ሰው ሁሉ ግፉን ይመለከተው ዘንድ ከልዩ ልዩ ቋንቋ ወደ ዓረብኛ ተተርጉሞ ከዓረብ ወደ እንግሊዝኛ፣ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በሦስት ቋንቋ ታትሞ እንዲወጣ አድርጌ አለሁ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ። (ሐተታ) ኢትዮጵያ አገራችን በሥጋዊ ነፃነቷ ሆነ በሃይማኖታዊ ተግባሯ በቅዱሳት መጻሕፍትና በዓለም ታሪክ ላይ ከፍ ያለ የቀደምትነት ዝና ያላት በጣም የምታከራ ሰላማዊትና ሃይማኖታዊት ሀገር ናት ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሀገረ ሰላም የምትባለዋ ኢየሩሳሌም ወደሷ የተላኩትን የነቢያትንም ደም ስታፈስ የኖረች ይህ ቀረው የማይባል ኃጢአትና የግፍ ግፍ ተግባር የተፈጸመበት ሀገር መሆኗን የተጻፉት መጻሕፍትና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "እነሆ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ

መቅደስና በመሠውያው መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ እንደሚደርስባችሁ እውነት እላ ችኋለሁ ይህ ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ነቢያትን የምትገድል ወደርሷ የተላኩትንም የምትወግር,, ሲል ይነግረናል፣ ማቴ፡ ፳፫-፴፯። የቀሩትም ዓለማት እንደዚሁ በነቢያትና በሐዋርያት ላይ የፈጸሙትን የደም ማፍሰስ ተግባር ገድለ ሐዋርያት ይነግረናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን ያንድ ነቢይ ወይም ያንድ ጻድቅ ደም ያልፈሰሰባት ንጽሕትና ቅድስት ሀገር በመሆኗ ሀገረ ሰላም መባል የሚገባት ኢትዮጵያን ነበር። የኢትዮጵያ ሰላማዊነት ማስረጃ፤

<u>አንደኛ</u>፡ የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ልትረዳ መጣች ተብሎ እንደተጻፈው ሌሎች አገሮች ከጨለማ ወደ ብርሃን ሲመልሷቸው ለጥቅማቸው የሚመጡላቸው ሐዋርያትን የሚገድሉ ሲሆኑ፣ የኢትዮጵያ ንግሥት ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብን ለመረዳት ስትሻ ከኢትዮጵያ ተነሥታ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ መምጣቷን ፩ ነገሥት ፲ ፩፡ ዜና መዋዕል ካልእ ፱ ፩። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ "ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረድበታለች፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፣ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ,,፣ ብሎ ኢትዮጵያ እምነት በጐደለባቸው በሌሎች ሕዝቦች ላይ ትፈርዳለች ሲል አመስግኖ በመለኮታዊ ቃል ከፍ አድርጎ በሌላው ዓለም ላይ ፈራጅ ሲያደርጋት ከመስማት የበለጠ ክብርና ቅድስና አይገኝም፣ ማቴ፡ ፲፪ ፵፪።።

<u>ሁለተኛ</u>፡ ሌላ ዓለማት የወንጌልን የምሥራች ሊያበሥሩዋቸው የተላኩትን ሐዋርያት የምሥራቹን አንቀበልም ብለው እኩሉን በሰይፍ እየገደሉ እኩሉን በእሳት እያቃጠሉ እኩሉን በመስቀል እየሰቀሉ ንጹሕ ደም በማፍሰስ ልዩ ልዩ ግፍ በሚፈጽሙበት ጊዜ ኢትዮጵያ ያንድ ሰው ደም ሳታፈስ የንግሥት ህንደኬ መላክተኛ መስፍን ኢየሩሳሌም ድረስ መጥቶ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ (ሰው) መሆን ሰምቶ የወንጌልን የምሥራች ተቀብሎ በሐዋርያው እጅ ተጠምቆ ያመጣላትን የሐዲስ ኪዳንን እምነት በዘመነ ሐዋርያት መቀበሏን በሐዲስ ኪዳን በመላው ዓለም ዘንድ ሲነበብ ይኖራል፣ የሐ. ሥራ. ፰፡ ፳፯ ።

<u>ሦስተኛ</u>፡ ከንግሥት ህንደኬ መላክተኛ መስፍን የተቀበለችውን የወንጌልን እምነት ለመረዳትና የክርስቶስን ሃይማኖት በሀገሯ ላይ ለመዘርጋት፣ ቅዱስ ፍሬ-ምናጦስን ልከ ሥርዓተ ክህነት አምጥታ ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጢረ ቍርባንን እግብታ ትምህርቱን ከሌላ ሰትሻው ራሷን በራሷ በማስተማር የፈጸመችው የሃይማኖት ስብከት መስፋፋት ተግባር፣ ባዕድ ሰው ያልደከመባት፣ ጻማ ባዕድ ያልተቀላቀለባት ሰላማዊት ሀገር ናትና፣ እንደ እውነቱ ሀገረ ሰላም መባል የሚገባት ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት ቢባል እውነት ነው እንጂ ራስን ማሞጋገስ አይደለም ።

አራተኛ፡ በላይኛው መሥመር እንደተነገረው ፃማ በዕድ በልተቀላቀለበት ሴላ ነጋሪ ሰትሻ ብሉይ ኪዳንን በንግሥተ ሳባ፡ ሐዲስ ኪዳንን በህንደኬ ንግሥት መላክተኛ ተቀ ብላ ከቆየች በኋላ አራተኛ መቶ ዘመን ሲጀመር ትምህርተ ሃይማኖትንም ከሣቴ ብር ሃን ብላ ከሰየመችው ከቅዱስ ፍሬ-ምናጦስ ሰምታ የሐዲስ ኪዳንን ስብከት ከስፋች በኋላ ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ፍቅር ቅናት የተናደዱ ኢትዮጵያውያን መናንያን ፍቅረ ዓለምን እየጠሉ በሱዳንና በምድረ ግብጽ በረኻው እያቋረጡ ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው በቅዱሳት መካናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ በሠራ በቸው ሥፍራዎች እየወደቁ እየተነሡ በመላው ዓለማት ፊት ያሳዩትን የሃይማኖት ተጋድሎ ተግባር የተመለከቱ ጐብኝዎች ፡ አንዳንዱ አብሲኒያን ፡ አንዳንዱም ኖቢያን ፡ አንዳንዱም እንዳያን እያሉ እንደዛሬው ዘመን የዓለም ካርታ ባልታወቀበት ጊዜ ፡ የሃይማኖት ፍቅራቸውን ትሕትናቸውንና ደግነታቸውን በማድነቅ አስፋፍተው ጽፈ ውት ይገኛል ። እነዚህ የኢትዮጵያ መናንያን ከምስተኛ መቶ ዓመተ ምሕረት ጀምረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ በሠራባቸው በቅዱሳት መካናት ገዳማት አቅንተው ማኅበር ሠርተው ከገሪክ አርቶዶክስ ማኅበር በተቀር ሌላ ክርስቲያን ሳይቀድማቸው በቅዱሳት መካናት ባለርስት ባለመብት ሆነው በቀደምትነት የሚኖሩ መሆናቸውን ለመ ረዳት መጽሐፉን መመልከት ነው ። እነዚህ መናንያን መነኮሳት በኢየሩሳሌም ይህን የመ ሰሉ ገዳማት አቅንተው በመካናት ቅዱሳት የሃይማኖት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ የኖሩት እንደነ አጼ ዘርአ-ያዕቆብ ያሉ ደጋግ ነገሥታትና ፡ አንዳንድ ምእመናን ለነፍሳ ቸው ሲሉ በምጽዋት ከሚቸርዋቸው እርዳታ በተቀር በራሳቸው ገድልና ትሩፋት ሥራ ጽረው ግረው ከሚያገኙት የዕለት ምግብና ከዓመት ልብስ በቀር እንደ ዛሬ ዘመን ሁሉ ለገዳሙ መረጃ የሚሆን ርስት ጉልት አልነበራቸውም ። ለምሳሌ ስለ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከተጻፈው ታሪክ ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኛል ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፡ በኩሉ ልብየ ዘኪያሁ አመ ልክ፡ በኩሉ ኀይልየ ወበኩሉ ነፍስየ ወበኩሉ ሕሊናየ ዘበቱ አሰምክ፡ ዘእጉዝ በሐብለ አምልኮቱ ዘኢይትበተክ ዘበቱ አሐዩ ለዝሉፉ ወኢይትህወክ ። ተጽሕፈት ዛቲ መል እክት ውስተ ዛቲ መጽሐፈ ሲኖዶስ እምኀቤየ እምኀበ ዘርአ ያዕቆብ ዘስመ መንግሥ ትየ ቈስጠንጢኖስ እምአመ አንበረኒ አምላክ እስራኤል በብዝኀ ምሕረቱ ዲበ መንበረ መንግሥተ ኢትዮጵያ በ፷ ዓመት እንዘ ሀሎኩ ውስተ ሀገረ ሸዋ እንተ ትሰመይ ተጉ ለት ፡ ትብጻሕ ኀበ ፍቁራንየ ማኅበረ ቅዱሳን እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ሀገር ቅድ ስት በሰላመ እግዚአብሔር አሜን ።

አስተበፅዓክሙ ፈድፋደ ፡ ቀዳሚ ኩንክሙ ፂዉዋነ ለቃለ ወንጌል ዘይቤ ዘኢኀደገ አብሁ ወእሞ ወብእሲቶ ወውሉዶ ወገራውሂሁ ወኵሎ ዘበ፡ ወበእንተዝ ኀደግሙ ዓለመ ወበእክሙ ውስተ አርዐተ ምንኵስና ፡ ወዳግመ ፂወወክሙ ቃለ ነቢይ ዘይቤ ኢይበውእ ውስተ ጽላሎተ ቤትየ ወኢየዓርግ ውስተ ዓራተ ምስካብየ ፡ ወኢይሁበን ንዋመ ለአዕይ

ንትየ ወኢድቃሰ ለቀራንብትየ ፡ እስከ እረክብ መካኖ ለእግዚአብሔር ፡ ወማኅደሮ ለአ
ምላክ ያዕቆብ ።

ወበእንተዝ አጥበዕክሙ ለነጊደ ኢየሩሳሌም ሀገሩ ለንጉሥ ዐቢይ ፡ እንዘ ኢትፈ
ርሁ ምንዳቤ ፍኖት ሐሩረ መዓልት ወቀሪ ሌሊት ወቀትለ ፈያት ። ወሶበ በጻሕክሙ
ሀየ ተፈጸመ ላዕሌክሙ ዘተብህለ በነቢይ "ንበውእ እንከሰ ውስተ አብያቲሁ ለእግዚአብ
ሔር ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ,, ፡ ወከፈለክሙ ከመ ተአምኑ
መካናቲሁ ቅዱሳተ እመክነ ቍጽረቱ እስከ መክነ ዕርገቱ ፡ ወበእንተዝ እነሂ እትአመን
በጸሎትክሙ ወበኵሉ ምንዳቤክሙ በእንተ ፍቅረ አምላክ ዘበጽሐክሙ እምሥርወ
ልብየ ፡ እኤምኅክሙ እንዘ እብል ሰላም ለክሙ ደቂቀ ኢትዮጵያ ዘዜወወተክሙ ኢየሩ
ሳሌም ምድራዊት ከመ ታብጽሕክሙ ኀበ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ፡ ሰላም ለሃይማኖት
ክሙ እንተ በሥላሴ ፍጽምት ወለምንኵስናክሙ አምሳለ መላእክት ።

ሰላም ለእጋሪክሙ እለ ኬዳ ፡ ወለአእዳዊክሙ እለ ጐድጕዳ ፡ ወለከናፍሪክሙ እለ
ሰዐማ በከመ ፈቀዳ ፡ ወለአዕይንቲክሙ ነጽሮ እለ አግሃዳ ፡ ገሊላሃ ኀበ ተሰብአ ወቤተል
ሔምሃ ኀበ ተወልደ አምላክነ ነሢአ ዘዚአነ ጠባይዐ ፡ ወጎለሃ ኀበ ሰክበ ወተፀን
ግዐ ፡ ናዝሬትሃ ኀበ ተሐፅነ ወዮርዳኖስሃ ኀበ ተጠምቀ ከመ ያንጽሐነ ፡ ቆሮንቶስሃ ኀ
በ ጸመ በእንቲአነ ፡ ቀራንዮሃ ኀበ ተሰቅለ ከመ ይቤዝወነ ፡ ወጎልጎታሃ ኀበ ተቀብረ
ወተንሥአ ከመ ያሕይወነ ፡ ደብረ ዘይትሃ ኀበ ዓርገ እምህየ ኀበ አቡሁ እምላክነ ከመ
ያብአነ ውስተ ውሰጤ መንጦላዕት አርያማዊ ኀበ በአ ለሊሁ ሐዋርያነ ዘእምቅድሜነ ፡
ጽርሐ ጽዮን ኀበ ወረደ ጸራቅሊጦስ ኀበ ሐዋርያት አበዊነ ።

ወሰላም ካዕበ ለአዕይንቲክሙ እለ ነጸራ ብርሃነ ፡ ዘይወፅእ እመቃብሪሁ ለእግዚእነ
በቀዳሚት ሰንበት ዘውእቱ መኑትወ ፋሲካነ ። ሰላምክሙ ወፍቅርክሙ ጸሎትክሙ
ወበረከትክሙ የሀሉ ምስሌየ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ናሁ ፈኖኩ ለክሙ ዘንተ መጽሐፈ ሲኖዶስ ከመ ትትናዘዙ ባቲ በቀዳሚት ሰንበት
ወበእሑድ ከመ ይኩነኒ ተዝካረ በኀቤክሙ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ይእዜኒ ሠራዕኩ ለክሙ አነ ዘርአ ያዕቆብ ዘስመ መንግሥትየ ቈስጠንጢኖስ እም
አመ አንበረኒ እግዚአብሔር ዲበ መንበረ መንግሥት እምአመ ንግሥየ በ፷ ዓመት እም
ድረ ዝበላ ወእመንፈቁ ዘይወፅእ ግብሩ በ፪ ዓመት ፪ ሕልቀ ወርቅ ከመ ይኩኖሙ ሲ
ሳዮሙ ወዓራዘሙ ለማኅበረ ኢየሩሳሌም ወህብኩ ከመ ይኩን ተዝካርየ ወለተዝክረ እ
ግዝእትየ ማርያም ። ወግበሩ በዓላ ለባሕቲትየ አመ ፩ ለግንቦት ልደታ ወአመ ፳ወ፩
ለጥር ዕረፍታ ። አመ ፲ወ፯ ለነሐሴ ፍልሰታ ፡ ወበዓለ ወልዳሂ እግዚእነ ኢየሱስ ክር
ስቶስ አመ ፳ወ፱ ለታኅሣሥ በዘተወልደ ፡ ወግበሩ በቤተልሔም በዓለ ፋሲካ ዝውእቱ
ትንሣኤ ሞቱ ማሕየዊት ፡ ወካዕበ አክብሩ ኵሎ በዓላቲሃ ለእግዝእትነ ማርያም ዘሀሎ
ውስተ መጽሐፈ ተአምሪሃ ፴ወ፪ ወዓዲ ከመ ታኅትዉ ሊተ ቀናዲለ ውስተ መቃብረ
እግዚእነ ፩ ፡ ወበውስተ አንቀጸ ዴዴሁ ፩ ፡ በየማኑ ፩ ፡ ወበፀጋሙ ፩ ፡ ወኀበ ግንዘቱ ፫ ፡

ወበጎበሂ ርእየቶ መግደላዊት ፩፡ ጎበ ሀይከል ዘዚአነ ፪፡ ወካዕበ ጎበ ዝጎራ ለእግዝእትነ ማርያም በጌቴሴማን ፫፡ ጎበ ተወልደሂ እግዚእነ በቤተልሔም ፩፡ ወጎበ ዓርገ እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ፩፡ ከመዝ አጎትዉ በንዋየ ዚአየ ወትረ ወኢታብጥሉ ወኢትደምሩ ንዋየ ካልእ፡ እስመ ኦነ እጉዝ በሐብለ ፍቅርክሙ፡ ጸሎትክሙ ወበረ ከትክሙ የሀሉ ምስሌየ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

አፍቁራንየ ኢትበሉ ለባሕቲትነ ይወርድ ብርሃን ከመ ኢይኩን ተመክሖ ላዕሌክሙ እስመ እንትሙ ተአምሩ ከመ ተመክሖ ያመጽእ እኩያተ ወትሕትና ያመጽእ ሠናያተ፡ ሰላም ለክሙ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌክሙ አሜን ።

<u>ትርጓሜ ው፤</u> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ፡ በፍጹም ልቡና ዬ እሱን የማመልከው፡ በፍጹም ኃይሌ፡ በፍጹም ነፍሴና በፍጹም ሕሊናዬ እምጠጋ በት በማይበጠስ እምልኮቱ ገመድ የተያዝሁ ለዘለዓለሙ እሱን በማመን ሳልታወክ በምኖርበት ባንድ አምላክ ስም አምኜ ይህችን ደብዳቤ እጽፍላችሁ አለሁ ።

ይህች ደብዳቤ ስመ መንግሥቴ ቄስጠንጢኖስ በሆነ በኔ በዘርአ ያዕቆብ እጅ ተጻ ፈች ። የእስራኤል አምላክ በቸርነቱ ብዛት በኢትዮጵያ መንግሥት ዙፋን በስቀመጠኝ በኟኖው ዓመት በሸዋ አውራጃ ውስጥ ተጉለት በምትባል (ወረዳ) ሳለሁ የተጻፈች ደብዳቤየ በእግዚአብሔር አንድነት፡ በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ወዳጆ ቼና ቅዱሳን ማኅበር ትድረስ ። አሜን (በእውነት) ።

መጀመሪያ ነገር፡እናት አባቱን፡ ሚስቱንና ልጆቹን፡ እርሻውንና ያለውን ሁሉ ያል ተወ ለሚለው ለወንጌል ቃል ምርኮኞች ሆናችኋልና እጅግ አመሰግናችኋለሁ ። ስለ ዚህም ዓለምን ትታችሁ በምንኵስና ቀንበር ውስጥ ተጠምዳችኋልና፡ዳግመኛም የእግ ዚአብሔር በታውን፡የያዕቆብ አምላክ ማደሪያውን እስክገኝ ድረስ ወደቤቴ ጥላ ውስጥ አልገባም ። ወደምኝታዬ አልጋ ላይም አልወጣም፡ ለዓይናቼም እንቅልፍን፡ ለቅንድ ቦቼም ሽልብታን አልሰጣቸውም ያለው የነቢዩ ቃል ማርኳችኋልና ስለዚህ የደገኛው ንጉሥ አገር ወደምትሆን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቄረጣችሁ።

በመንገዱ የሚገኘውን ልዩ ልዩ መከራንና የቀን ሐሩር የሌት ቍርን የወንበዴዎ ችን አደጋ ሳትፈሩ ለመሄድ ቄረጣችሁ ።

ከዚያም በደረሳችሁ ጊዜ "እንግዲህ ወደ ቤቶቹ እንገባለን፡የጌታችንም እግር ከቆመበት እንሰግዳለን,, ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ቃል ፡ ለናንተ ተፈጸመላችሁ ።

ከተፀነሰበት ጀምሮ እስከ ዓረገበት ድረስ ያረፈባቸውን ቅዱሳት በታዎች እጅ ትነ ሡ ዘንድ አደላችሁ ። ስለዚህ እኔም ስለ አምላክ ፍቅር በደረሰባችሁ ጻዋትወ መከራና በጸሎታችሁ በፍጹም ልቡናዬ እታማመናለሁ ።

ምድራዊዋ ኢየሩሳሌም ወደ ሰማያዊዋ ኢየሩሳሌም ታደርሳችሁ ዘንድ የማረክቻ ችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ፡ ለናንተ ሰላምታ ይገባል እያልኩ እጅ እነሣችኋለሁ ።

ፍጽምት በምትሆን ሦስትነት ለምታምን ሃይማኖታችሁም ሰላምታ ይገባል ። የመ ላእክት አምሳል ለምትሆን ምንኵስናችሁም ሰላምታ ይገባል ። ኢየሩሳሌም ለመሄድ

ለደከሙ እግሮቻችሁና ደጅ ለጸፉ እጆቻችሁ፡ እንደ ፍላጎታቸው ቤተ መቅደስን ለሳሙ ከንፈሮቻችሁ ሰላምታ ይገባቸዋል ።

ሰው የሆነበት ገሊላን ፡ አምላክ የኛን ባህርይ ባሕርይ አድርጎ የተወለደበት ቤተ ልሔምንና የተጠጋበትና የተኛበት በረትን ፡ ያደገበት ናዝሬትን ፡ እኛን ከኃጢአት ያነጻን ዘንድ የተጠመቀበት ዮርዳኖስንና ስለኛ የጸመበት ገዳመ ቆሮንቶስን ፡ እኛን ለመታደግ የተሰቀለበት ቀራንዮንና እኛን ያነሣን ዘንድ ተቀብሮ የተነሣበት ጎልጎታን ፡ ሐዋርያችን አርሱ ፡ አስቀድሞ ወደ ገባበት አርያማዊ (ሉዓላዊ) ወደ ሚሆን ውሳጤ መንጠላዕተ እኛን ያገባን ዘንድ ወደ አባቱ ያረገበት ደብረ ዘይትንና ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ አባቶቻችን ሐዋርያት የወረደበት ጽርሐ ጽዮንን ፡ በግልጥ ለማየት ለበቁ ዓይኖቻችሁ ሰላምታ ይገባቸዋል ።

ደግሞም የፋሲካችን ዋዜማ በሆነችው በፊተኛይቱ ሰንበት ፡ ከጌታችን መቃብር ውስጥ የሚወጣውን ብርሃን ላዩ ዓይኖቻችሁ ሰላምታ ይገባል ። ሰላምታችሁና ፍቅራችሁ ፡ ጸሎታችሁና በረከታችሁ ለዘለዓለሙ ከኔ ጋር ይኑር (በኔ ላይ ይደር) አሜን (በእውነት) ።

ይኸውና ፡ በመጀመሪያይቱ ሰንበትና (ቅዳሜ) በአንደኛይቱ ሰንበት ትጽናኑበትና በናንተ ዘንድ ለዘለዓለም መታሰቢያ ይሆነኝ ዘንድ ይህን ደብዳቤ ጽፌ ላክሁላችሁ ።

አሁንም ስመ መንግሥቱ ቈስጠንጢኖስ የሆነ እኔ ዘርአ ያዕቆብ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ዙፋን ባስቀመጠኝ በኟኛው ዓመት የሚከተለውን ሠራሁላችሁ ።

ከዝበላ ወረዳ የሚወጣውን ግብር እኩሌታውን በሁለት በሁለት ዓመት አንዳንድ መዶ (ሕልቀ ወርቅ) የወርቅ ወጭት ምግባቸውንና ልብሳቸውን ይሆን ዘንድ በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ማኅበር ሠርቸላቸዋለሁ ።

ለኔ መታሰቢያ በእመቤታችንና በኔ መካከል መታሰቢያ ሆኖ ይኖር ዘንድ ፡ የልደታ በዓል በሚከበርበት ግንቦት ፭ ቀን ፡ ያረፈችበት ጥር ፳፩ ቀን ፡ በዓለ ፍልሰታ የሚከበርበት ነሐሴ ፲፮ ቀንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት በሚውልበት ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በቤተ ልሔም አድርጉ ።

እንዲሁም ማሕየዊ ከሚሆን ከሞቱ የተነሣበትን የፋሲካን በዓል አክብሩ ። ዳግመኛም ፡ በተአምረ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ፴፪ የእመቤታችንን በዓላቶች አክብሩ።

ደግሞም ፡ ጌታችን በተቀበረበት መቃብር ላይ አንድ መብራት ፡ በቀኙና በግራው በሚገኙ ደጃፎች አንዳንድ መብራቶች ፡ ከተገነዘበት ላይ አንድ ፡ ማርያም መግደላዊት ጌታችን ካየችበት በታ ላይ አንድ ፡ በኛው ሃይከል ላይ ሦስት ፡ እመቤታችን በተቀበረችበት በጌቴሴማን ሦስት ፡ ጌታችን በተወለደበት በቤተ ልሔም አንድ ፡ ጌታችን ካረገበት ደብረ ዘይት ላይ አንዳንድ መብራቶች ዘወትር በኔው ገንዘብ አብሩባቸው ፡ አታስታጉሉ ። የሌላን ገንዘብ ወይም መብራት አትጨምሩ ። እኔ በገመድ ፍቅራችሁ የተያዝኩ ኔኛና ፡ ጸሎታችሁ ፡ ልመናችሁና በረከታችሁ ለዘለዓለሙ በኔ ይደር ፡ አሜን (በእውነት)።

ወዳጆቼ ሆይ! መመካት እንዳይሆንባችሁ ለኛ ብቻ ነው ብርሃን የሚወርድልን አትበሉ። ትምክህት፣ ክፉ ነገርን እንደሚያስከትል፣ ትሕትና ግን በጎ ነገርን እንደ ሚያመጣ እናንተ ታውቃላችሁና።

ሰላም ለናንተ ይሁን፣ የእግዚአብሔር ፍቅርና አንድነት ከናንተ ጋራ ይኑር። አሜን፣ (በእውነት)።

እንደዚሁም፣ እንደ ኤ. ቍ. በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ሕዝበ ክርስ ቲያን ገንዘብ መጥቶላቸው በቅዱሳት መካናት የነበራቸውን መቅደሶችና ገዳማት እንዳሳ ደሱ በ፲፻ው ማስረጃ ተጽፎ ይገኛል። እንደ ታሪክ ነገሥቱ፣ ዘመኑ በአጼ ልብነ ድንግል ጊዜ ነው። እነዚህ ማኅበረ መነኮሳት እንደዚሁ ከኢትዮጵያ ነገሥታትና ምእመናን በሚ ደርሳቸው ምጽዋት እየተደገፉ ሲኖሩ ከግራኝ ጦርነት ወዲህ የቱርክ መንግሥት እንደ ጠላት አይቶ ችላ ስላላቸው ከኢትዮጵያም እርዳታ ስላቋረጠባቸው በድኩም ላይ ሳሉ በኢትዮጵያችን ዘመነ መሳፍንት በሚባለው ዘመን ከአስራ ሰባተኛው መቶ ዘመን ወደ ዚህ ደግሞ የባሰውን ፍጹም ድህነት ደርሶባቸው በቅዱስ መቃብር (በጎልጎታ) ውስጥ የነበራቸውን የርስት መብት ለአርመኖች ለቀው ዴር ሥልጣን ከሚባለው ከጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ጋር በምሥራቃዊ ክፍል በኩል ገጥሞ ከሚገኘው ገዳማቸው ብቻ ተወስነው ሠፈሩ። ከዚህ በኋላ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሚገኘው የኢትዮ ጵያ ንብረት ሁሉ ለአርመኖች ተሰቆ ስለ ነበር የግሪክ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ንብረት ከአርመን እጅ መውደቅ አይገባውም ሲል፣ ተቃውሞ በሁለቱ ማኅበሮች በግሪክና በአ ርመን መካከል በኢትዮጵያ ንብረት ምክንያትና በየጊዜው የተፈጠረው ትግል ልክ የለውም።

ቀጥሎም አብዛኛውን ንብረታቸውን ለቀው በዴር ሥልጣን ገዳም ውስጥ ሲኖሩ በአሥራ ሰባተኛ መቶ ዘመን ማለቂያ (፲፯፻፫) ዓ. ም. ግድም መዓልም አብራሂም (ኢብራሂም ዠሕሪ) የሚባል ግብጻዊ ሰው ስምንት አገልጋይ (ባሮች) ይዘ ዴር ሥል ጣን ገዳም ደርሶ ወደ መነኮሳቱ መጥቶ አባቶቼ የሃይማኖት ወንድማችሁ ነኝ በከተማው ቤት ስለ አጣሁ አባካችሁን ከእናንተ በታ ማረፊያ ስጡኝ አላቸውና መነኮሳቱም አጽ ፋቸውን ለብሰው ጸሎት ከማድረግ በተቀር የሰውን ተንኰል የማያውቁ ደጋግ መነኮ ሳት ነበሩና ፈቅደውለት ከገዳማቸው ገባ። መዓልም አብራሂም ዠሕሪም የተማረ ሰው ነበረና በኢየሩሳሌም ከቱርክ መንግሥት ሥራ አግኝቶ ከፍ ያለ ባለ ሥልጣን ሆነ። በመነኮሳቱም ላይ ሠለጠነና ለነሱ ተጠያቂ ነኝ እስከ ማለት ደርሶ ከቤታቸው ከፍሎ ይስ ሐቅ ቤይ ለሚባል ሰው በኪራይ ሸጦ ወዲያውም አንድ ካህን ስደዱልኝ ብሎ ወደ ግብጽ ልኮ ቀሲስ ጊዮርጊስ የሚባለውን ሕጋዊ ቄስ ላኩለትና በገዳሙ አስገባው። አብራሂም ዠሕሪ ሲያልፍም፣ ቀሲስ ጊዮርጊስ በሱ ሥፍራ ለገዳሙ ዋና እኔ ነኝ ብሎ ተተክና እን ዲያውም ከዴር ሥልጣን ገዳም ቦታ ከፍሎ ምሥራቁን ክፍል ለመስኮቦች ሸጠ፣ መነ ኮሳቱ ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ጥቃታቸውን የሚገልጹበት ቋንቋ ባለማወቃቸው የመጣ ግብ

ጳዊ የኛ ጥገኞች ናቸው እያሉ ያንገላቷቸው ጀመር ። ከዚህ የበሰውን ደግሞ ፲፰፻፹ ዓ. ም. ቤቱን እናሳድሰዋለንና ልቀቁ ብሎ ከነጓዛቸው ከመኖሪያ ቤታቸው አስወጣቻ ውና ከታደሰም በኋላ ተመልሰው እንዳይገቡ አድርገዋቸው ዛሬ የኛ መነኮሳት ከሚገ ኙት ዋና ሥፍራ ውስጥ ብቻ ተወስነው ቀሩና ዋናውን የኢትዮጵያ ገዳም ግን ግብ ጾች በተንኰል ገብተው እስካሁንም ይዘዉታል ። የኛ መነኮሳት ግን ሥፍራቸውን ለቀው መውደቂያ ቢያጡ በዚሁ ባሉበት ቦታ ያሽከከ ዋሻ የመሰሳለ የጭቃ ጕጅ እያ በጁ መቀመጥ ግድ ሆነባቸው ። እንዲሁም ሆነው በመከራና በሥቃይ ሥፍራ ሲኖሩም ፲፰፻፸፰ ዓ. ም. የወረርሽን (ተስቦ) በሽታ ገብቶ የኢትዮጵያን መነኮሳት አንድ ሳይቀር በሽታው ጨረሳቸውና አሁንም ግብጾች ጊዜው ረድቷቸው የገዳሙን መክፈቻ ፈጽመው እጅ አደረጉና በተላላፊ በሽታ አመካኝተው በኢትዮጵያውያን ቤተ መዛግ ብት (ዕቃ ቤት) ውስጥ የነበረውን የርስት ማስረጃ ኩሻንና (ከርታ) ቅዱሳት መጻ ሕፍት የመላበትን ግምጃ ቤት በሙሉ በእሳት አቃጠሉት ። በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም ገዥ ኢብራሂም ፓሻ የምሥር ሰው በመሆኑም ደህና አጋጣሚ አገኙና የፈቃደቸውን ለመ ሥራት ተመቻቸው ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ከፕቶች ዴር ሥልጣን የሚባለው ገዳም የከ ፕቶች ርስት ነው እንጂ የሐበሾች አይደለም ማለትን ደፍረው ለመናገር የቻሉት ። ይህንንም ቃጠሎውን ለመረዳት የእንግሊዝ ቆንሲል ፊንና ቢሾፕ ጐባት ከመንግሥታ ቸው ጋር የተጻጻፉትን ዜና ኢትዮጵያ በሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም ከሚባለው ፩ኛ መጽሐፍ ውስጥ መመልከት ይጠቅማል ፡ ከዚህም በተቀር በኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳም ያለውን ታሪክ ተመልከት ፡ በዚህ ጊዜ ራስ ዓሊና ደጃዝማች ውቤ ቀጥሎም አጼ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥትና ለእስክንድርያም ፓትርያርክ ተጻጽፈው ነበር ። ይሁን እንጂ የተፈጸመ ነገር የለም ።

አ ፄ ዮ ሐ ን ስ

አጼ ዮሐንስ በነገሡ ጊዜ ይህን የዜጎቻቸውን ጥቃት ለማስወገድ ብዙ ሥራ ሠርተዋል ከሥራቸውም አንዱ የኢትዮጵያ መነኮሳት መጠጊያ ሥፍራና መድረሻ እጥተው የአርመን ገዳም ጥግ አድርገው ለዕለት ራት እየተገዙ ወራዳ ኑሮ መኖራቸ ውን ሰምተው ከአርመን ጥገኝነት ተለዩ እንጂ ለናንተ መሆን አያቅትኝም ብለው የጻፉት ደብደቤ እንደሚያስረዳው በየጊዜው ስማኅበሩ ቀለብ ይልኩት የነበረው ገንዘብ ልክ የለውም ። ይህም ብቻ ሳይሆን ሰፊ መሬት ገዝተው ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መነኮሳትም የውሀ ጕድጓድም (ቢር) አሠርተው ማኅበሩ በነፃነት የሚኖሩበት ገዳም ሠርተዋል ፤ ደግሞም ጉራዕ ላይ በደረጉት በቱርኮች ጦርነት ከምርኮ የተገኘውን ፮ ሣጥን ሙሉ ወርቅ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ማኅበር መረጃ ይሁን ብለው ልከዋል ። የሳጥኑም ምልክት እስካሁን ይገኛል ።

አፄ ምኒልክ።

አፄ ምኒልክም በነገሡ ጊዜም በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ዜጎቻቸው ማኅበረ መነኮሳት የደር ሥልጣን ገዳም መክፈቻ በግብጾች እጅ ከተያዘ በኋላ፡ በውስጡ የሚኖሩትን መነኮሳት በሩን ቄልፈው መግቢያና መውጫ እያሰጡ ቤተ ክርስቲያናቸውንም ዘግተው የሃይማኖት አገልግሎት እንዳይፈጽሙ በማድረግ የሚፈጽሙበቸውን ስቃይና የሚሠሩበቸውን ግፍ በሰሙ ጊዜ በ፲፱፻፩ ዓ.ም. ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን ልከው ከቱርክ ሥልጣን ዓብደልሐሚድ ጋር በመላላክ የዴር ሥልጣን ገዳምን ቍልፍ ለማስመለስ ብዙ ሠርተው ነበር። ነገር ግን፡ ግብጾች በተንኰል ከኢየሩሳሌም ገዥ ጋር ተመሳጥረው ከ ሡልጣኑ የተላለፈውን ትእዛዝ ከተግባር እንዳይውል ቢያደርጉበቸውም ደጃዝማች መ ሸሻ በርትተው የኢትዮጵያ መነኮሳት በነፃ የሚጠቀሙበትን ከዴር ሥልጣን በምሥ ራቅ በኩል አዲስ በር አስከፍተዋል።

ስለ ዴር ሥልጣን ገዳምና ግብጾች ስለ ዘጉዋቸውም አርባዕቱ እንስሳንና ቅዱስ ሚካኤልን ሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ርስት ጉዳይም ፡ በኢየሩሳሌም ከሚገኙት የሃይ ማኖት ባለሥልጣኖችና ከነዋሪ ሕዝበ ክርስቲያኖችም በምስክርነት ቃል ጠይቀው የሰበ ሰቡዋቸውን ጠቃሚ ማስረጃዎች ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጽሕፈት ሚኒስቴር ሐር ሽቫ ተገኝተው ይኸውና ለዛሬው ክርክራችን ዋና ጠቃሚ ሆነው በዚሁ መጽሐፍ ው ስጥ ከ፱ እስከ ፲፩ኛ ቍጥር ክልሼ የተጻፉት ማስረጃዎች ናቸው።

አፄ ምኒልክ ከዚህም ይበልጥ የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንን በፄ ዮሐንስ ሞት የተቋረጠውን ሥራ አስፈጽመዋል። ለማኅበሩ መረጃ መተዳደሪያ የሚሆን (200.000) ሁለት መቶ ሺ ማርያ ትሬዛ ብር በንክ አግብተው የሚከራይ ቤት ሠርተው ማኅበሩ ራሳቸውን ችለው በደምብ እንዲተዳደሩ አድርገዋል።

እቴጌ ጣይቱም በተለይ መሬት ገዝተው ከፍ ያለ ኪራይ የሚከራዩ ቤቶች አሠር ተው እጅግ ጠቃሚ የሆነ እርዳታ አድርገዋል።

ከዚህም ሌላ በየጊዜአቸው ፡ ለኢየሩሳሌም ማኅበር መረጃ ርስትና ቤት የሰጡ የሚከ ተሉት ናቸው። ክቡር ራስ ወልዴ ፤ ክቡር አፈ ንጉሥ ነሲቡ ፤ ክቡር ደጃዝማች ባልቻ ፡ ክብርት ወይዘሮ ደስታ ፡ እነዚህ ጌቶች ሁሉም በታ ገዝተው ቤት ሠርተው በመስጠት ለገዳሙ ታላቅ እርዳታ አድርገዋል።

አፄ ኃይለ ሥላሴ።

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፡ ገና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን ሲባሉ በ፲፱፻፲፯ ዓ-ም ኢትዮጵያን ከተ ባበሩት የዓለም መንግሥታት ማኅበር በገቡበት ዘመን ኢየሩሳሌም መዋተው ለኢትዮ ጵያ ገዳም አንድ ዘውድ አበርክተው ተመልሰዋል። ከዚህም ሌላ ኢየሩሳሌም በአይሁድ ና በዓረቦች መካከል በ፲፱፻፵፯ ዓ-ም፡ በተነሣው ጦርነት ምክንያት በኢየሩሳሌም የሚገ

ኙት የኢትዮጵያ ገዳማት ንብረታቸው ሁሉም ተበላሽቶ ችግር ስለ ደረሰባቸው ገዳማቱ እንዳይጠፉ አስበው ከኢትዮጵያ መረጃ ገንዘብ እንዲሰጣቸው አዝዘው ይኸውና በመ ት በመቱ ከኢትዮጵያ ን. ነገሥት መንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴር ብዙ ገንዘብ እየተላከ ላቸው ማኅበሩ እንዲረዱ አድርገዋል ። ከዚህም ሌላ ደግሞ ጥንት የክርስቲያን መቃ ብር በታ የነበረው በጦርነት ተይዘ ገዳማቱ የሚቀብሩበት ሥፍራ ቢያጡ አልአዛር ከሞት ከተነሣበት ከተማ ዳር ፲፪ ሺሕ ካሬሜትር መሬት አስገዝተው በኢየሩሳሌም የሚ ኖረው ሕዝባቸው እንዲቀበርበት ፈቅደው በብዙ ሺሕ ብር ቅጥሩን አስቀጥረው ሰጥተዋ ል ፣ ወደፊትም ረጅም ዕድሜ ይስጣቸው እንጂ በግርማዊነታቸው ያለን ተስፋ ብዙ ነው ።

እቴጌ መነን ።

ግርማዊት እቴጌ መነን እኒህ ብፅዕት ንግሥት ለኢየሩሳሌም ያደረጉት እርዳታ እ ጅግ ብዙ ነው ።

አንደኛ በ፲፱፻፲፩ ዓ-ም ልዕልት ወይዘሮ መነን ሲ ባሉ ኢየሩሳሌም መጥተው ለማኅበሩ ብዙ የልብስና የገንዘብ እርዳታ አድርገው አንድ በለፈርጥ የከበረ የዕንቊ አክ ሊልና ንዋየ ቅድሳት ለኢትዮጵያ ገዳም ሰጥተው ተመለሱ ።

ሁለተኛ ደግሞ ፣ በዮርዳኖስ የሚኖሩት የኢትዮጵያ መነኮሳት መኖሪያ ቤትና ቤተ ክርስቲያን ሳይኖራቸው በየጫካው ውስጥ የሳር ጐጆ ቀልሰው በንዳድ በሽታ እየተሰ ቃዩ ሲኖሩ የነበሩትን ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን ቤተ ክርስቲያንና ቤተ ማኅበሩን ባንድ ሕንፃ አያይዘው ታላቅ ገዳም አሠርተው ቤተ ክርስቲያኑን በቅዱስ ሥላሴ ስም በ፲፱፻፳፩ ዓ-ም አስባርከው ሰጥተዋል ። እነሆ ዛሬ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ካሉት የክርስቲያን ማኅ በሮች የኢትዮጵያን ገዳም የመሰለ ዝግጅት ያለው ገዳም አይገኝም ። ከዚህም ሌላ ዛሬ ም ለዚሁ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ላሠሩት ገዳም መረጃና ለሕንፃው መጠበቂያ የሚ ሆን በኪራይ የሚረዳ ቤትም ባዲስ አበባ ከተማ ላይ በማሥራት ይገኛሉ ።

(ወይዘሮ አማረች ዋለሉ) እኒህ የተባረኩ ወይዘሮ አማረች ገና ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በሕይወታቸው ሳሉ ጣዕመ ዓለምን ንቀው መንነው ወደ ኢየሩሳሌም መጥ ተው በተቻላቸው ሁሉ ችግረኛን እየረዱ እስከሁን ኢየሩሳሌም ተቀምጠው በሕይወት ይገኛሉ ። ለኢየሩሳሌም ገዳም ከኢያሪኮ ከተማ አታክልትና ቤት ያለበት ገነት የሆነ ፫ ሺህ ፬፻ ካሬ ሜትር ያህል ጥሩ በታ ገዝተው ለዮርዳኖስ ሥላሴ ቤተ ክርስቲ ያን መረጃ ይሁንልኝ ብለው ሰጥተዋል ።

ማ ሳ ሰ ብ ።

ይህ ዓለም የሰው ዘር ሁሉ እየታየ የሚያልፍበት መተላለፊያ ጐዳና ነው እንጂ ማንም አይኖርበትና ጥቂት ዘመናት ቢኖርም ቅደም ተከተሉን የጥርጊያውን ተራ ወረ ፋውን የመጠበቅ ያህል ቆይቶ በተራው ሁሉም መንገደኛ ስለሆነ እስኪያልፍ ድረስ እግረ መንገዱን እንደየዕድሉ እግዚአብሔር የከፈለውን ያህል ደግ ቢሆን ወይም ክፉ

የተቻለውን ሠርቶ የጉዞው ተራ ሲደርስ እሱው ራሱ አላፊ ሃያጅ ነውና ባላፊው ጊዜ የማያልፍ ደግ ሥራን የሚሠራ ሰው ቅዱስ የመባል የክብር ስም ይወርሳል ።

ምስጋና ፡ በዚህ በሥራ መቅድም ላይ ቀደምት ሆነው ለተከታዮቻቸው የማኅበራዊ ኑሮ አብነት ሆነው ገዳማቱን ላቀኑልንና የሥራ መሪ ማስታወሻ ትተው ያለፉትንና ቃን ቋውን በማያውቁት በሀገር ቅድስት በኢየሩሳሌም ረኃቡንና ጽምኡን ታግሠው ለኢት ዮጵያ ትውልድ በቅዱሳት መካናት ይህን የመሰለ የሃይማኖትና የቅድስና መታሰቢያ ዝክረ ነገር የሆነውን ሥፍራ ትተውልን ያለፉት ብፁዓን አበው መነኮሳትን አስቀድሚ አመሰግናለሁ ።

እንደዚሁም ዛሬም በዘመናችን ይህን በቅዱስ ሥፍራ መብት ከክርስቲያን ማኅበ ሮች ጋር በተለየም ደግሞ በዴር ሥልጣን ገዳም ርስትነት ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ማኅ በርና በኮፕቶች መካከል ከጥንት ከአበው የተወረሰውን ታላቅ ጥቃት ከኢትዮጵያውያን ትከሻ ላይ አውርዶ ለመጣል የሐሳብ ተካፋይ ሆነው በብዙ ትጋትና በቅንነት ከኮፕቶች ጋር ያለውን ታላቅ ትግል ሲታገሉ የሚገኙትን የኢየሩሳሌምን ኑዋሪ ማኅበሮችና ከመንግ ሥት በለሥልጣኖችም በኢየሩሳሌም የቆንስልነት ሥራ ይዘው ይህን አውን እሳትመን የምናወጣውን ጽሑፍ በመፈለግ የረዱትን አቶ ሐዲስ ዓለማዮሁን ፡ አቶ ሠረቀ ብርሃን ገብረ-እግዚእንና በሎንዶን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አምባሳደር የነበሩት ከቡር አቶ አበበ ረታንም በኢየሩሳሌም ያልተገኙትን አሌክስ ዲባደን የጻፈውን ታሪክና የእንግ ሊዝ ባለ ሥልጣኖች በቅዱሱ ሥፍራ ስላለው የኢትዮጵያ መብት በኢየሩሳሌም ከ፲፰፻፱ እስከ ፲፰፻፷፯ የሚለውን ማስረጃ ከለንደን ሚዜዩም በመፈለግ ስለረዱን፡ ሁሉንም በሳ ዩት መልካም ፈቃድና በሠሩት አገልግሎት አመሰግናቸዋለሁ ።

በመጨረሻ ለመቅድም ንግግሬ ማሠርያ አግዚአብሔር ባይፈጥረን በዓለሙ ላይ በመ ኖር ፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መርጠው ባይልኩንም ሁላችንም ለሥራ ባልተገኘንም ነበርና በሰማያት ለእግዚአብሔር ፡ በምድርም መልካም ፈቃድ ላላቸው ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምስጋና ይሁን ስል መቅድሙን አቆ ማለሁ ።

"ወዘንተ ኵሎ ገቢረክሙ በሉ አግብርት ጽሩዓን ንሕነ ፡ ወዘይደልወነ ለገቢር ገበርነ,, ሉቃ. ፲፯ ፡ ፲ ፡ እናንተ ደግሞ፡ እንደዚሁ የታዘዛችሁትን ሁሉ ሠርታችሁ ሥራ ፈት ባሮ ች ነን ልንሠራው የሚገባንን አድርገናል በሉ ።

አባ ፊልጶስ ።

መ ግ ቢ ያ ።

ኢየሩሳሌም በእጁ እንድትወድቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተፈቅዶለት ድል ከደረገ በኋላ ፣ የአማኞቹ መስፍን ተብሎ የሚጠራው ከሊፋ ዑመር አ.ብን አልኽታብ አሚር አልማዕሙኒን ፣ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ክርስቲያኖች በሰጠው ትልቁና ታሪካዊ ቃል ኪዳኑ (ያማራይት ክቨናንት) ተጽፎ እንደተገለጸው ሁሉ ፣ የኢትዮጵያ ማኅበር ከጥንት ዘመናት ጀምሮ በቅዱስ መካን አካባቢ ውስጥ ሰፍሮ የቀረ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ይኽ ቃል-ኪዳን ከሌላው ጽሑፍ ላይ በመጨመር " በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩት ሌሎች ክርስቲያኖችም ማለት ጆርዳውያንና (ኩርዶች) ኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) እንደዚሁም ቅዱስ መካንን ለመጐብኘት የሚመጡት ኤውሮጳውያን ፣ ኮፕቶች ፣ አሶራውያን ፣ አርመኖች ፣ ኔስቶራውያን ፣ ያዕቆባውያንና ማሮኒታውያን . . . . . ,, እያለ ይጠቅሳል ። ስለዚህ እስላሞች ኢየሩሳሌምን ድል ከማድረጋቸው በፊት ኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) በሀገሩ ላይ በቀደምትነት የሚኖሩ እንጅ እንደሌሎቹ ሕዝቦች ለመጐብኘት ብቻ የሚመጡ ያለመሆናቸውን ቃል-ኪዳኑ በግልጽ ያስረዳል ያሳያልም ።

ኢትዮጵያ በመካን ቅዱስ ከሚገኙት ዋና ዋና አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በኢየሩሳሌም ከቅዱስ መቃብር (ጎልጎታ) ፣ በቤተልሔም ጌታ ከተወለደበት ቤተ ክርስቲያን ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም (ጌቴሴማኒ) ቤተ ክርስቲያንና ከሱልጣኑም ገዳም (ዴር ኤል ሱልጣን) ሌላ ፣ በተጨማሪ በቅዱስ መቃብር ዙሪያ ላይ አያሌ አብያተ ክርስቲያናትና መጸለያ ነዋሪ ቦታዎች ስለ ነበሩዋት የኢትዮጵያ ማኅበር በሀገሩ ላይ ርስት ይዞ ከኖረው ባለንብረት ሕዝብ አንዱ ክፍል ነበር ።

ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ ማኅበር ከቤኒ ዑስማን (የቱርክ ነገሥታት) ከሊፋዎች ስለ ነዋሪው ሕዝብ መብትና ይዞታ የታወጀውን መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ፣ እንዲሁም ማስረጃ የሚሆኑ ሰነዶችና የሱልጣኑን ንጉሣዊ አዋጆች በእጅ ይዞ ቢገኝም ቅሉ ፣ አሁን በዚህ መግቢያ ውስጥ መግለጽ ባያሻኝም ፣ ከዘመን ብዛት የተነሣ ጭቅጭቅና ያልታሰበ ታሪካዊ መለዋወጥ ስለ ተፈጠረ ፣ ሰፊው የኢትዮጵያን ይዞታ መቀነስ ጀመረ ። ከሌሎቹ ወገኖች ይልቅ መንፈሳዊ እምነታችን የመነጨበት የኮፕት ቤተ ክርስቲያን በርስታችን ውስጥ ስለ ገባችብን በቅዱስ መካን የነበረው ይዞታችን በጣም እያነሰ ኼደ ።

ባለፉት አያሌ ዓመታት ውስጥ ነገሩ እንዲመረመርልንና ዳኝነትም እንዳታይልን ለባለሥልጣኖቹ በማመልከት ፣ ጥንታዊ መብታችንና ይዞታችን እንዲመለስልን ጠይቀን ስለ ነበር ፣ ጳለስጢናን በሞግዚትነት ያስተዳድር የነበረው እንግሊዛዊ ሥልጣን

ጉዳዩን በዓለም መንግሥታት ማኅበር ትእዛዙ ለሚቋቋመው ከሚሲዮን እንዲቀርብ ከመሰነ በኋላ ከሥልጣኑ ስለ ለቀቀ ፡ ጉዳዩ እፍጻሜ ሳይደርስ ቀርቷል ።


አሁን ግን የአገሩ አስተዳደር ወደ ሐሸሚታዊው የዓረብ መንግሥት አገዛዝ ዘሮ ሊለሚገኝ ፡ የግርማዊው ሐሸሚት መንግሥት በነገሩ አስፈላጊውን ምርመራ በመፈጸም ጉዳትና በደል የደረሰበት ማኅበራችን ፡ ፍርድ እንዲያገኝ ያደርግልን ዘንድ ታላቅ ተስፋና እምነት ጥለንበታል ።

አሁን በእጃችን ከሚገኙት የመብታችን ማስረጃዎችና ሰነዶች ውስጥ በዚሁ መጽሐፍ በከፊል የምናሳትምበት ምክንያትና ሐሳብም ፡ ተመልካቹ ሕዝብና ባለሥልጣኖቹ እንዲያውቁት ሲሆን ፡ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም ጉዳዩን ለሚመለከት ባለሥልጣን ተጨማሪ ማስረጃዎች ለማቅረብ ዝግጁ ነን ።

ኢትዮጵያውያን በክብርና በሥነ ሥርዓት ተጠብቀን እንድንኖር ከመጀመሪያው የእስላም ሑጅራ (ስደት) በኋላ በደግነቱ ባዘዘልንና በደነገገልን በታላቁ የዓረቦች ነቢይ ታል (ው.ል) መሠረት ፡ የጆርዳን መንግሥትና ሕዝቡም በግቡ እንዲሰማን በጥልቅ እየ ተማመንን እግዚአብሔርም ረዳታችን ሆኖ ሐሳባችንን እንዲባርክልን እንጸልያለን ።

በእግዚአብሔር ጸጋ ፡ በኢየሩሳሌም መንበር ፡
በሐሸሚታዊው የጆርዳን መንግሥትና በማእከላዊ ምሥራቅ ፡
ኢትዮጵያዊ ጳጳስ አባ ፊልጶስ ዘኢየሩሳሌም ።

አንደኛው ክማስረጃ ።



በመሐሪው እግዚአብሔር ስም

አንደኛው ማስረጃ።

የቡመር ቃል-ኪዳን።

እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲጠብቀው ከምንሻ
ከቡመር ኢብን አልኽታብ የተሰጠው አዋጅ ግልባጭ።

እስላምነትን ለሰጠን፥ በሃይማኖቱ ላከበረንና ነቢዩ መሐመድን በቸርነቱ ላስነሣልን ቀናውን መንገድ ላሳየን፥ ከተበተንም በኋላ አንድ ላደረገን ለልቦችን ኅብረትን ለሰጠንና በጠላቶቻችንም ላይ የድል አድራጊነትን ክብር በማግኘት የአህጉር ገዢነትን እንድንቀዳጅና ጥብቅ ተፋቃሪዎች እንድንሆን ላደረገን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው፥ ሰላምና በረከቱም ለነቢዩ መሐመድ ይሁን። እግዚአብሔርን የምታመልኩ ሁሉ ለዚህ አምላካዊ ጸጋ የሚገባውን ምስጋና ለእግዚአብሔር አቅርቡ።

እኔ ቡመር ኢብን አልኽታብ መኖሪያው በኢየሩሳሌማዊት ደብረ ዘይት ለሆነው እጅግ ለተከበረውና ለታላቁ የመለካይት ሃይማኖት ፓትርያርክ ለብፁዕ ሰርፎርንዮስ ይኸንን መልእክቴን (ጽሑፌን) ቃል-ኪዳንና ሕጋዊ ውል አድርጌ በመስጠት እጽንቼለታለሁ። ይህም ቃል-ኪዳን ለሕዝቦች ለካህናት ለመነኮሳትና እንዲሁም ለመነኮሰይያት በያሉበት ሰላምና ጸጥታ ያገኙበት ዘንድ ዙሚ የተባለው የጸጥታ አስከባሪነት ደንባችን በሚያዘው መሠረት፥ የሕዝብ ደህንነትና ጸጥታ በእኛ በአማኞችና በተከታዮቻችን ሁሉ እንዲጠበቅ የሚያስገድዱ ስለ ሆኑ፥ ሕዝቦች ታዛዥነትና ትሕትና እንደማሳየታቸው መጠን በሚችግራቸው ሁሉ ፍርድ ያገኙበታል። ለሕይወታቸው ለአብያተ ክርስቲያኖቻቸውና ለገዳሞቻቸው እንደዚሁም በጌታ መቃብር ውስጥ ሆነ በውጭ፥ ጌታ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተልሔምና በታላቁ ቤተ ክርስቲያን፥ ቀጥሎም በዋሻው ሥስት ማዕዘናት፥ ማለት በደቡብ፥ በሰሜንና በምዕራብ ሆነው በይዘታቸው በሚገኙት በሮችና ቅዱሳት መካናት ሁሉ ተጠበቂነትና ደኅንነት ያገኙበታል። ይኽ ውል በሀገሩ ለሚኖሩት ለሌሎቹ ክርስቲያን ዜጎች ማለት ለጆርጃውያንና (ኩርዶች) ለኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) እንደዚሁም ለመገበኘት ለሚመጡት ኤውሮጳውያን ለኮፕቶች፥ ለአርመኖች፥ ለኔስቶራውያን፥ ለያዕቆባውያንና የፓትርያርኩም ተከታዮች ለሆኑት ማሮኒታውያን ሁሉ በኅብረት ያገለግላል። ሌሎቹም ዜጎች ሁሉ በታላቁና በደጉ ነቢይ በተወዳጁ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ዘንድ፥ በሕግ እንዲጠበቁና ደህንነትም እንዲያገኙ በእጁ ጽሕፈት በታዘዘላቸው መሠረት እኛ አማኞቹና ምእመናኖቹ ትእዛዙን አክብረን በሥነ ሥርዓት የምንጠብቃቸው ናቸው። እላይ የተጠቀሰው ፓትርያርክ ግን ከሁሉም ይበልጥ ቅድሚያና የበላይነት መብት አለው።

ሆኖም ሕዝቦቹ የመሬት ግብር ሆነ የዘበኛ አበል፥ እንደዚሁም ማናቸውም ሌላ ዓይ

ነት ቀረጥ እንዳይከፍሉ ነፃ አድርገናቸዋል። ወደ ቅዱስ መቃብርም ሆነ፡ ወደ ሌሎች ቅዱሳት መካናት ሲገቡ እንዲሁም በምድር ወይም በባሕር ሲጓዙ መንገላታት ወይም መከሰስ ሳይደርስባቸውና ሌላም ነገር ሳይጠየቁ በደህንነትና በሰላም እንዲኖሩ አድርገናል። ቅዱስ መቃብሩን ለመጐብኘት (ለመሳለም) ተፈቅዶላቸው የሚገቡት ሌሎች ክርስቲያኖች ግን እላይ ስሙ ለተጠቀሰው ፓትርያርክ ሚሶ የብር ድራሕም እያንዳንዳቸው ይከፍላሉ። ይኽ አዋጆቹን ፓትርያርኩ በሀገሩ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን ገዢና ባለመብት ሆኖ እንዲያስተዳድር የሾምንበት ስለሆነ፡ እያንዳንዱ አማኝ ወንድ ወይም ሴት እንደ ዚሁም ከእስላሞች ሰጋዲያን ወገን ባለጸጋ ወይም ድኻ የሆነ ሁሉ ወንድና ሴት ሳይ ቀር ትእዛዙን ለማክበርና ለመጠበቅ ይገደዳል። ይኽ አዋጃችን ታላላቆቹና የተከበሩት የነቢዩ በልንጀሮች ማለት እነዓብዱላ ዑስማን ኢብን ዓፋን፡ ስዒድ ኢብን ዜድ፡ ዓብደልራሕማን ዒብን ዑፍና የቀሩትም ታላላቅና የተከበሩት ደቀ መዝሙሮቹ ባሉበት ታውጆ ተሰጠ። ይኽ አዋጅ ሕጉን ባጸናንለት ሰው በኩል ተጠብቆ ክብር ያለውና የጸና ትእዛዛችን ሆኖ እንዲታወቅ አዘናል።

ልዑል እግዚአብሔር መሐመድ ጌታችንን ከዘሮቹና ከደቀ መዝሙሮቹ ጋር ይበር ክልን፡ የሁለቱ ዓለማት ጌታ ለሆነው እግዚአብሔርም ምስጋና ይድረሰው። እግዚአብሔር ገዢአችን ነውና በረከቱ ከእንደራሴው ጋር ይሁን።

፰ ራቢዕ አልዓወል፡ በ፲፩ የነቢይ ሒጂራ ተጻፈ።

ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ማናቸውም አማኝ ይኽን አዋጃችንን አንብቦ ቢቃወም የእግዚአብሔርን ቃል-ኪዳን እንዳፈረሰና መልእክተኛውንም እንደ ተቃወመ ይቈጠርበታል።

ሁለተኛው ማስረጃ።

ከሡልጣን ሱለማን የተሰጠ አዋጅ።

ሕያውና ቅዱስ በሆነው በአንድ አምላክ ስም፥ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያዊው አባ ሐኒስ ትጋት በ፲፩፻ ዓ-ም መታደስ ጀመረ። የማደሻውም ገንዘብ ከግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ከኢትዮጵያውያን ምእ መናን ዘንድ የተላከ ነው።

ኢትዮጵያውያን ስለ ርስቶቻቸውና ስለ ገዳሞቻቸው ስለ ቅዱሳን ስፍራዎቻቸው፥ እንዲሁም በቅዱስ መቃብር ቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ ስላሉት ቤተ መቅደሶ ቻቸው ማስረጃ የሚሆኑ ፊርማዎችና አዋጅም የተነገረባቸው ሸሐኒ የተባሉ ንጉሣዊ ድንጋጌዎች በእጃቸው ይዘዋል። ከዚህም በላይ የኢትዮጵያውያን ይዞታ የራሳቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ስለ ሥርዓተ ጸሎታቸውና በተለይም በኢየሩሳሌም ስላለው ንብረታቸው ከዚህ በታች የተመለከተው ጽሑፍ ያስታውቅላቸዋል።


በመካነ ግንዘቱ ድንጋይ ላይ ሰባት ቀንዲሎች የሚንጠለጠሉበት ቦታ፥ በጌታ መቃብርም ውስጥ እሳት ከሚያቀጣጥሉበት ስፍራ፤ አንደኛው በደቡብ፥ አንደኛው በሰሜን ሆኖ ሌሎችም ሰባት ቀንዲሎች ከሚንጠለጠሉበት ቦታ፥ ከቤተ ክርስቲያኑ በስ ተደቡብ የሚገኙት ሦስት (ደጃፍ) የኢትዮጵያውያን በሮች ከነብርጭቆ መብራታቸው ሦስት (ደጃፍ) በስተሰሜን በሮች በድርብ ሳንቃ የተሠራው ክፍል፥ እላይ ከተጠቀ ሰው ቤተ መቅደስ በስተምሥራቅና በመካነ መቃብሩ መካከል ያለው መቅደስ በሳንቃ ታንጸ ከቅዱስ ትክል ድንጋይ በላይ ተገጥሞ የሚገኘው መዝጊያ ከነብርጭቆ መብ ራቱና ከነፍርግርጉ ሳንቃ መጋረጃው በሙሉ ጠቅልሎ የነርሱ ንብረት ስለሆነ ማንም በኢየሩሳሌም የሚገኝ ሌላ ክርስቲያን ማኅበር ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ንብረቶች ላይ የሚቃወም አለኝ የሚል የለም።

ከዚህም ሌላ በስተደቡብ በኩል በቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን የሚያጋናኝ ሆኖ በሩ በስተደቡብ በኩል የሚከፈተው ታችኛው የኢትዮጵያውያን ቤተ መቅደስና በመ ካነ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን በር በኩል የሚገባው የሡልጣን ገዳም (ዴር ሡልጣን) ከነቤቶቹና ከነመኖሪያዎቹ የኢትዮጵያውያን ንብረት ነው።

ልብሰ-ተክህኖ የሚቀመጥበት ትልቅ ሣጥን ከነይዞታውና በሡልጣኑም ገዳም (ዴር ኤል ሡልጣን) ላይኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ንብረትና ብዙ መጻሕፍት በሙሉ፥ እንደዚሁም በሡልጣኑ ገዳም (ዴር ኤል ሡልጣን) አጠገብ የሚገኘው የቅ ድስት ኢሌኒ ቤተ ክርስቲያን ጭምር የነርሱ ነው።

ሡልጣን ሣሊም።

ሁለተኛው ማስረጃ ።



ይኽ ድንጋጌ በእጇ የተሠራ ቡሩክ ትእዛዜ ስለሆነና መጽናትም የሚገባው ስለሆነ ማናቸውም ሰው ሳይጠብቀው ቢቀር የእግዚአብሔር የቍጣ ሰይፍ ይወድቅበታል ።

የልዑል እግዚአብሔር ረድኤትና በተወደደው ነቢዩ ፣ የእግዚአብሔር ቅድስት ከተማ ወደሆነችው ወደ ኢየሩሳሌም ዛሬ በ፲፩ኛው ሰፈር በ፫፻፶፯ኛው የሔጂራ ዘመን በ፲፩፻፲፯ ዓ-ም ገብቼ ገዢ ሆኜ አለሁ ።

ስሙ እዚሁ ግርጌ የተመለከተው ክቡር የሸሪዓ ዳኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ እውቀት እንዲሰጠው እየተመኘሁ ፣ ይኽንን እጅግ የተከበረውን ንጉሣዊ ድንጋጌ በኢየሩሳሌም በሚገኘው የሸሪዓ ፍርድ ቤት መዝገቡ እንዲመዘገብና ድንጋጌውም ጸንቶ የተከበረ እንዲሆን ያደርግ ዘንድ አዝዣለሁ ። በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያውያን እንደራሴ ማስረጃውን (መብቱን) ባስፈለገ ጊዜ ሁሉ ለመከራከር እንዲችሉበት ተመዝግቦ እንዲሰጠው ጠይቋል ።

መስከረም ፲፩፻፱ ዓ-ም ተሠራ ።

ፊርማና የእማኞች ፊርማ
ሡልጣን ሱሌማን ።

<u>ከፎቶግራፍ የተቀዳ ነው ።</u>

ይኽ ግልባጭ ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘሩ ሰዎች በሉበት ተሠጠ ፤

፩ኛ ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ገዳም — አባ ዓብደል መሲሕ ኢትዮጵያዊ ፤

፪ኛ ከግሪክ አርቶዶክስ ገዳም — ፓትርያርክ ጀማኖስ ጽርዓዊ ፣

፫ኛ ከአርመኖች አርቶዶክስ ገዳም — ሣርኪስ አርመናዊ ፤

፬ኛ ከሸኽ ሙስተፋ ዘካርያ — የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ፤

፭ኛ ከሸኽ ኑር ኤዲንና ሐሰን ፓሻ — የጳለስጢና ጠቅላይ ገዢ ፤

፮ኛ ከክቡር ዳኛ ጀላቢ ኢብን አልባሕኒ — ከሸኽ መሐመድ ኢብን ኤልሸኽ ዓብደልቃድር አልሸሪፍ ኢብን አልሸኽ ሞሒ ኤዲን አልነካል ኤል ሻፊ — ሸኽ ኤል ኢስላምና የሃገር ቅድስት ሙፍት የነበሩት ፤

፯ኛ ከዛሬው ሙስጣፋ ፓሻ ።

ከዋናው የቱርክ ጽሑፍ በትክክል የተቀዳ መሆኑን አረጋግጣለሁ ።

ማኅተም ዓ-ም

የኢየሩሳሌም እንደራሴና
ሰበት ሌላ ፊርማዎች ።

ሦስተኛው ማስረጃ ።


በኢየሩሳሌም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ። — የመዝገብ ቁጥር ፻፺፩ — ገጽ ፯ ።


በታላቁ ጌታ ፊት የአዋቂዎች አዋቂ፣ የሕግ ትክክለኛ አስተርጓሚና ዋና አስፈጻሚ፣ በእስላሞች ዘንድ ትክክለኛ ዳኛ፣ በምድር ከፍተኛ ባለሥልጣን፣ የዕውቀትና የሐሳብ መፍለቂያ፣ የታላቁ ነቢይ ፍኖተ-ትምህርት ወራሽ፣ የዳኞች ዳኛ፣ የሕግ ባለሥልጣንና የዓለማዊው ችግር ፈች፣ የሐቀኝነት ገላጭ፣ እጅግ ከፍተኛና ገናና መንፈሳዊ፣ በሠለጠኑት ምድራውያን አካባቢዎች ዘንድ እጅግ የተሞገሰ፣ በእስላሞች ዘንድ የሸኽች ሊቅ፣ የተከለከለውና የሕጋዊው ምግባር ልዩ አዋቂ፣ የመልካምና የመጥፎ ነገር ሚዛን የሆነው የሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኛ እጅግ የተከበረው ዓብደል ራሒም፣ በዚህ ውል ላይ ከንዱን ጭኖ ፈርሞበታል ። ክብሩና ሞገሱ ለዘለዓለም ይኑር ።

ዛሬ በኢየሩሳሌም የሚኖረው በግሪክ ክርስቲያኖች ፓትርያርክ በብፁዕ አባ ባይ ሶስ ፊት ቀርቦ ክብረ መንግሥቱ ለዘለቄታው እንዲኖር የምንመኝለትን የተከበረውንና ከፍተኛ የሆነውን የሱልጣን ድንጋጌ (አዋጅ) ከማጎተሙ ዘውድ ጋር አቀረበልን ። ትእዛዙም በከፍተኛው የእስላሞች ዳኛና በአንዱ አምላክ ብቻ በሚያምኑት ምእመናን ዘንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆኖ የከብርና የሐቀኝነት ምንጭ እንደዚሁም ለሕዝብ ሁሉና ለኢየሩሳሌም ቃዲና፣ የሕግ አስከባሪ በሆነው ዳኛ አድራሻነት የተጻፈ ነው ።

ይኽ አዋጅ የወጣበት ምክንያት በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የሚኖሩት ያላመኑ የግሪክ ክርስቲያን ተወላጆች ከዚህ በታች የተጻፈውን አቤቱታ ለግርማዊ ንጉሥ ስለ አቀረቡ ነው ።

አቤቱታ ። ለሱልጣን አሕመድ ኻን ዋቅፍ እንዲከፈል የተወሰነብንን ግብር በመክፈል ረገድ ምንም ጉድለት ሳይኖርብንና፣ ከንጉሣዊውም ድል ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከፍተኛና የተከበሩ ትእዛዞች፣ የፍርድ መዝገቦችና (የሸሪዓ ሐኝ) የነቢዩም ታላላቅ ደቀ መዝሙሮች፣ በዘመኑ ማንም ሰው እንዳይከራከረን ያገዱበት ቃል-ኪዳን በእጃችን እያለ፣ በደማስቆ የሚገኙት ገዢዎችና ገንዘብ አስገቢ ሹማምንቶች (ደፍተር ዶር) ገንዘብ ከፈሉ እያሉ ግብር ሰብሳቢዎቻቸውን በየጊዜው ወደ ገዳሞቻችን ስለሚልኩብን ይኽ የገንዘብ አጠያየቃቸው ለሸሪዓውና (መንፈሳዊ ሕግ) ለፍትሐ ብሔሩ ሕግ፣ እንደዚሁም በደጉቹ በነቢዩ ደቀ መዝሙሮች ለተሰጠን ቃል-ኪዳን ተቃራኒ ሆኖ ብናል ። ከዚህም ሌላ የተጠቀሱት ገዢዎችና የደማስቆ ገንዘብ አስገቢ ሹማምንቶች ከአርባና ከሠላሳ ቀን በማይበልጥ ጊዜ እየመጡ እርዳታ ይጠይቁናል ። የተከለከለውን ገንዘብ ከሕግ ውጭ የሆነውን ኟውን በአንድ አሰድ ፒያስተር ሒሣብ ከመቀበላቸው ሌላ ፴ውን ሕገወጥ ገንዘብ በአንድ አሰድ ፒያስተር ሒሣብ አንዲመነዘር ያደርጉብናል ። በአምስት ፒያስተር ብቻ የሚገዛውን ልብሰ-ደማስቆ ፴ ፒያስተር ሒሣብ ያስከፍሉናል ። አንድ ቀሩና ስንዴ በገበያ ዓሥር መሥሪያ (ገንዘብ) ሲሸጥ እነርሱ ግን አንድ


المحكمة الشرعية



ቍና ሁለት ፒያስተር ሒሣብ እንድንከፍላቸው ያስገድዱናል ። ይኸውም ሁሉ የሚፈጸምብን በኃይልና በዓመፅ ነው ።

እንደ ዘምዘም (የሚክ ምንጭ) አድርገን ወደምናስከብረው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በያመቱ ለመጠመቅ ስንወርድ ፣ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በተለመደው መሠረት ለኢየሩሳሌም ገዢ በአንዱ ሰው ሦስት አሰድ ፒያስተር ሒሳብ እንከፍል ነበር ። አሁን ግን ከዚህ የበለጠ ምንም ተከፍሎ የማይታወቅ ሲሆን ከተለመደው በላይ ለመክፈል ይጠይቁናል ። ይኸውም በእያንዳንዱ ሰው ፬ ፒያስተር በተጨማሪ እንዲከፈል የሚጠይቅ ሲሆን ፣ ሌላም ብዙ የዓመፅና ሕገ-ወጥ ተግባሮች ይፈጽሙብናል ።

ይበልጡንም የግሪክኮች ፓትርያርክ ከኸሊፋ ዑመርና (ነፍሱን ይማር) እንደዚሁም ከጥንታውያኖችና ከአሁኖቹ ሱልጣኖች ጊዜ ጀምሮ የወጡትን ንጉሣዊ አዋጆችና ጽኑ ሰነዶች እንዲሁም የውል ማስረጃዎችን የያዘ መሆኑ ስለሚታወቅ ለጆርጃውያንና (ኩርዶች) ለኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) የተሰጡትን ርስቶች ጨምሮ ፣ በኢየሩሳሌም ቅዱስ መቃብር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የግሪክኮች ቦታና ገዳማትን እንዲይዝና እንዲጠብቅ በዚህም ይዘታ ማንም ክርስቲያን ክፍል እንዳይከራከረን ታዘልን የኖረ ሲሆን አሁን የደማስቆ አገረ ገዢዎችና ግብር አስገቢ ሹማምንቶች በሚልኩብን ሠራተኞቻቸው ምክንያት የመብታችን ተቃዋሚዎች ሆነውብናል ።

ከዚህም በላይ በቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሜ ስዑር ቀን እሳቱ ሲቀጣጠልና ብርሃን ሲወጣ ጡዋፎቹ ሲበሩ እንደልማዳችን ቀንዲል ይዘን ከአርመኖችና ከኤውሮጳውያን እንዲሁም ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ሁሉ አስቀድመን በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ መዞር (ውደት ማድረግ) ልማዳችን ነው ። በቤተልሔም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ቦታ ላይ የሚገኘው የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ፣ የደቡብና የሰሜን በር ቁልፎች እንዲሁም በዋሻው ውስጥ የሚገኙት ቀንዲሎችና መብራቶች ሌላም ቤተ ክርስቲያኑን የሚመለከት ሁሉ የአትክልቱና የመቃብሩ ቦታዎች ከግሪክኮች በተቀር ሌላ ክርስቲያን አለኝ ብሎ የማይጠይቀው የግላችን ስለሆነ ፣ ግርማዊ ንጉሥ (ሱልጣን) ንጉሣዊ አዋጁን በማውጣት እላይ በዘረዘርነው መብታችን ሁሉ ማንም ሰው በማናቸውም ምክንያት እንዳይገባብን ያደርግልን ዘንድ በትሕትና እንለምናለን ።

<u>ትእዛዝ</u> ። የግሪክ ተወላጆች ከንጉሣዊ (ካኒ) ድል ጊዜ ጀምሮ ነፃ የሆኑበትና እስከ ፣ሬም ድረስ ማንም ሰው ቢሆን ሲከራከርበት ወይም ሁኔታውን በፍርድ አስተያየት ሊለወጥባቸው ያልቻለውን የታላቁን ሱልጣን አዋጆችና ታላላቁም የነቢዩ ደቀ መዝሙሮች የተስማሙባቸው የውል ሰነዶች ያሉዋቸው መሆኑን ተመልክተን ፣ ይኸንን ንጉሣዊ አዋጃችንን ስንሰጥ ማናቸውም ሰው በቀጥታ እንዲፈጽመው በማዘዝ ነው ።

በደማስቆ የሚገኙት አገረ ገዢዎችና ገንዘብ አስገቢ ሹማምንቶች (ደፍተር ዴር) እንደዚሁም ሌሎች ባለሥልጣኖች ወኪሎቻቸውን ወደ ግሪክ ተወላጆች እየላኩ ያለ ሕግ ገንዘብ ከመሰብሰብ እንዲከለከሉ እያስታወቅን ፣ በቅዱስ መቃብሩ ውስጥና በውጭ ዓሉትም ስፍራዎቻቸው እንዳይገቡባቸው አዝዘናል ። ከ፱ እና ከ፵ ቀን በማይበልጥ ጊ

ዜ ውስጥ የሚጠይቁዋቸውን እርዳታ ከልክለናል ። ፴ውን ሕገ-ወጥ ገንዘብ ስለ አንዱ አሰድ ፒያስተር ማስመንዘር የለባቸውም ፣ ኃይልና ዓመፅም በላያቸው ላይ መፈጸምና አምስት ፒያስተር የሚከፈልበትን ልብስ ፴ ፒያስተር ሒሣብ ማስከፈል የለባቸውም ። አሥር መስፈሪያ በቀኑና ስንዴ ሲከፈል ሁለት ፒያስተር ሒሣብ እንዳያስከፍሉዋቸውና ማናቸውንም ገንዘብ ያለ ሕግ በጭቆና እንዳይሰበስቡ አግደናል ።

አላይ የተጠቀሰው የቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም አብረው የሚገኙት የኢትዮጵያውያንና የጆርጃውያን የርስት ቦታዎች የግሪክ ተወላጆች አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሁሉ ፣ በግሪክ ፓትርያርክ ሥርዓት ሆነው መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን ፣ ወደፊት ማናቸውም በምትክነት የሚመጣ የግሪክ ፓትርያርክ ሁሉ ከከሊፋው መመርና (ነፍሱን ይማር) ከቀደምት ሱልጣኖች በተሠጡዋቸውና በተሠሩት የውል ማስረጃዎችና ስምምነቶች መሠረት መያዝ አለበት ። የግሪክ ፓትርያርክ ራሱ ወይም በወኪሉ ሥልጣን የጆርጃውያንንና የኢትዮጵያውያኖችን ርስቶች አጣምሮ የሚጠብቅ ሲሆን ፣ ማንም የሌላ ሃይማኖት ወገን በዚህ ረገድ ሊከራከራቸው አይችልም ።

የግሪክ ተወላጆች (ስሑት) የሃይማኖታቸውን ክብረ በዓላት እንደ ልማዳቸውና ታሪካቸው ሲፈጽሙ የደማስቆ አገረ ገዢዎችና ገንዘብ ሰብሳቢ ሹማምንቶች (ደፍተር ዳሪያ) ሊገቡባቸው አይችሉም ። ከዚህም ሌላ የቅዳሜ ስውር መብራቶች በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደልማዳቸው ሲቃጠልና ቀንዲሎችም ካበሩ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑን ሲዘጉ ማንም አርመናዊ ሆነ ኤውሮጳዊ እንደዚሁም ሌላ ወገን ቀድሟቸው ሊዘር አይፈቀድለትም ። ይኽውም የቅዳሜ ስውር መብራት ከበራ በኋላ በሚደረገው ክብረ በዓል አስቀድመው በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ መዘር ልማዳቸውና መብታቸው ስለሆነ ነው ።

በቤተ ልሔም ጌታ ክርስቶስ በተወለደበት ላይ በእጃቸው በሚገኘው ዋሻ ምክንያት ማንም ሰው ሊቃወማቸው የማይችል ሲሆን ፣ በቤተ ክርስቲያኑም ደቡባዊና ሰሜናዊ በሮች የሚገኙት ቁልፎችና መቅረዞች ፣ መብራቶችና ሁለቱ የእትክልት ቦታዎች ሌላም በውስጡ የሚገኝና ቤተ ክርስቲያኑን የሚመለከት ሁሉ የነርሱ ነው ።

ይኽ አዋጃችን በሁሉም ዘንድ ታውቆ እንዲሠራበት ያወጣነው ስለሆነ ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ከመኰንንኖቹና ከወታደሮቹ ፣ የሕዝብ መሪዎችና ነጋዴዎች እንደ ዚሁም ሌሎች ሁሉ ፣ የታላቁም የሱልጣን የወደብ ሹማምንቶችና (የአምሣ አለቆች ሲፓሒ ፣ ያንከርጃ) ፣ አገልጋዮች እንደዚሁም የማናቸው ሃይማኖት አባሎች ሁሉ በዚህ ረገድ ከግሪክች ጋር ቢከራከሩና አቤቱታ ቢያቀርቡልን የማይለወጥ ትእዛዛችን መሆኑን እናስታውቃለን ።

ይኽ ታላቅ አዋጃችን ከዛሬ ጀምሮ የጸና እንዲሆንና የመብትም ማስረጃ ይሆን ዘንድ በግሪክ ተወላጆች እጅ እንዲቀመጥ አዘናል ።

በዚል ታዕዳ ፲ኛ ቀን በሺሕ፰፬ ዓመት ላይ ተሠርቶ ተሰጠ ።

ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔ በረከት እንዳይለየው የምንሻው ክቡር የሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኛ ይኽንን ታላቅና ንጉሣዊ አዋጅ በኢየሩሳሌም በሚገኘው ሸሪዓ ፍ/ቤት መዝገባ

ቸው ውስጥ እንዲያሰፍሩና አዋጁም የጸና እንዲሆን ያደርጉ ዘንድ የታዘዙ ከመሆኑም በላይ ፣ የአርመን ወገኖች በክቡር ዳኛው በኩል ተጠርተው ከኢትዮጵያውያን ጋር ከመከራከር እንዲታገዱ ርስቶታቻቸውንም እንዲሰቁላቸው እንዲደረግና ኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) በንጉሣዊና በሱልጣን ሕግ መሠረት በያዙዋቸው ንብረቶች ምክንያት ያለ አገባብ እንዳይከራከሩዋቸው ማስጠንቀቂያ እንዲነገርላቸው ታዘአል ። ስለሆነም ክቡር የሽሬዓው ዳኛን ንጉሣዊው አዋጅ በተጠቀሰው ፤መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ ያኔ ውኑ አዘዙና ንጉሣዊውም አዋጅ በትእዛዙ መሠረት በኢየሩሳሌም ሽሬዓ ፍ/ቤት መዝገብ ውስጥ ሰፈረ ።

ወዲያው የተጠቀሱት ክቡር የሽሬዓ ፍ/ቤት ዳኛ ቀጥሎ የተመለከቱትን ባለሥል ጣኖች ማለት የአርመኖች ጳጳስ ወኪል የሆኑትን ዶኒከና የአርመኖች አስተርጓሚ የሆ ነውን ያዕቆብ የሐይዘር ልጅን አቅርበው እላይ የተጻፈውን ንጉሣዊ አዋጅ በማንበብ ትእዛዙን አስታወቁዋቸው ።

ክቡርነታቸውም (ዳኛው) ንጉሣዊው አዋጅ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን የግሪኮች ፓትርያርክ የኢትዮ ጵያውያንን ንብረቶች ጭምር የሚጠብቅና ማናቸውም ሌላ ሃይማኖት ወገን በዚህ ረገድ ጣልቃ ገብቶ ሊከራከር ወይም ሊያግዳቸው ያለመቻሉን ግልጽ አድርገው ከሰረ ዱዋቸው በኋላ ፣ የኢትዮጵያውያን ንብረት የሆኑትን በመካነ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ቅዱሳን ቦታዎችንና ፣ አንዱ መብራት በመካነ ግንዘቱ ድንጋይ ላይ የተንጠለጠለው ሆኖ ሰባቱ በቅዳሜ ስዑር እሳት ከሚያቀጣጥሉበት ክፍል ውስጥ የተ ንጠለጠሉ መብራቶቻቸውን በውስጣዊ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን መቃብሩንና ከእ ሳቱ መቀጣጠያ ክፍል ውጭም አንድ ፣ በደቡብ አንድ በስሜን ያሉትን መብራቶች እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙትን ቅዱሳን መካናትን በሮችን ፣ መቅ ደሶቻቸውንና ንዋየ ቅዱሳን በእንጨት የተሠሩ ወለሎችን በሙሉ ለኢትዮጵያውያን እንዲያስረክቡ የአርመንን ወኪሎች አዘዙ ።

ቀጥሎም ከጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የኢትዮጵያውያን ንብረትና መሰል የሆ ኑትን ገዳምና ንብረቶች ፣ መስቀሎች ፣ መጋረጃዎችና ንብረቶች በሙሉ ለኢትዮጵያው ያን እንዲያስረክቡአቸው አዘውላቸዋል ።

የክቡር ዳኛው ትእዛዝ ትክክለኛና መልካም ስለ ነበረ ፣ አርመኖቹ ንጉሣዊውን አዋጅ ፀታላቅ ትሕትና የተቀበሉት መሆናቸውንና በታዎቹንና የቤተ ክርስቲያኑን መብራቶች ሙሉ በትእዛዙ መሠረት ለግሪክ ተወላጆች የሚያስረክቡ መሆናቸውን ገለጹና ፣ ግሪኮቹ ክቡር የሽሬዓው ዳኛ በመረጡዋቸው ዳኞች አማካይነት እላይ የተጠቀሱትን የብር መብራቶች ተረክበው ኢትዮጵያውያን በሚያሳዩት ጥንት በታቸው እንዲንጠለጠሉ ክግድረጋቸው በላይ ፣ በሮቹንና መቅደሶቹን እንደዚሁም ንዋየ-ቅዱሳቱን በሙሉ አስ ረክበዋቸዋል ።

ንጉሣዊው አዋጅ በታዛርነት መፈጸሙን ለማስረዳትና ዝክረ ነገሩ እንዲታወቅ

ለማድረግ ያህል በሸሪዓው ዳኛ ታዘው ርክክቡን ያስፈጸሙት ዳኞች በዚሁ ቀን አንድ መዝገብ ከፍተው አፈጻጸሙን መዝግበዋል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ ርክክብ መዝገብ ላይ ከተመዘገበው በስ ተቀር ሌላ የብር መብራቶች መስቀሎችና የብር ዕቃዎች በመካነ መቃብሩ ቤተ ክርስቲ ያን አለኝ ወይም ቀረብኝ የምትለው የለም ። አርመኖችም በንጉሥ ሱልጣን አዋጅ መሠረት ኢትዮጵያውያንና ግሪኮችን በሚመለከቱት ነገሮችና በኢትዮጵያውያን ርስ ቶች እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥና ውጭ በሚገኙት መብራቶቻቸው መንጠል ጠያ ስፍራዎች በቅዱሳን መካኖቻቸውና በንዋየ ቅዱሳታቸው የተነሣ ከግሪኮች ጋር እንዳይከራከሩ አዋጁ በሕግ ያገዳቸው መሆኑን በማስረዳት ክቡር የሸሪዓው ዳኛ አዝዘዋል ።

በዚል ሐ/ጃ ፲ኛ ቀን በሺሕ ፱፮ የሑጁራ ዘመን ተሠርቶ ተሠጠ ።

ስለ ትክክለኛ ግልባጭ ፡-

፻፱ የጆርዳን መንግሥት
ቴምብሮች ።

ራቢ አወል ፬ ቀን ፲፫፻፹፩ ሐ.ጁ.ራ ፡ — ፫-፲፪-፲፱፻፺፩ ዓ. ም.

ፌርማ ፡ ሐ.ሚ ሙሐ/ሲብ
የኢየሩሳሌም ሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኛ ።

ማኅተም ፡ የኢየሩሳሌም ሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኛ
ፌርማ ፡ ዋስፊ ቡዴሪ
ዋና ጸሐፊ ።


ከዋናው መዝገብ የተቀዳ ትክክለኛ ግልባጭ ስለመሆኑ ፡
የመዝገብ ቁጥር ፻፶፩ ፡ ገጽ ፯ ፡
ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ. ም.

ፌርማ ፡ ሙ/ላክ ሙሐ/ሲብ
ዋና ጸሐፊ ።

የመዝገብ መገልበጫ አንድ ዴናር በገንዘብ ደረሰኝ
(ቫውቸር) ቁጥር 3121/494683 ስለ መክፈሉ

ፌርማ ፡ ዋስፊ ቡዴሪ
ዋና ጸሐፊ ።

የኢየሩሳሌም ሸሪዓ ፍርድ ቤት ማኅተም ።



አራተኛው ማስረጃ ።

ለክቡር ደጃዝማች መሸሻ በይ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ጄኔራል ።

ክቡር ሆይ ፤

በኢየሩሳሌም ውስጥ በቅዱስ መቃብር ቤተ ክርስቲያን (ጎልጎታ) በስተምሥራቅ ገጥሞ ፥ የኢትዮጵያ መነኩሳት ስለሚኖሩበት ዴር ኤል ሡልጣን (ሡልጣን ገዳም) ስለ ተባለው ገዳምና ፥ ስለንብረትነቱም ባለቤትነት በኢትዮጵያ መነኩሳትና ኮፕቶች መካ ከል ስለ ተፈጠረው ክርክር ፥ ያለንን አስተያየት እንድንገልጽልዎ ተስፋ በማድረግ የጻ ፉት (የክቡርነትዎ) ደብዳቤ ስለ ደረሰን ፥ ቀጥሎ የተመለከተውን መልስ እናቀርብለን ።

የኢትዮጵያ መነኩሳት በጥንት ዘመን ወደዚሁ ገዳም የገቡበት ጊዜ አይታወቅም ፥ ይሁን እንጂ በሡልጣን ገዳም (ዴር ሡልጣን) አካባቢ ፥ በአቡነ አብርሃም ገዳም ውስጥ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ግማሹና (ግማሹ የግሪክ ሆኖ ቀሪው በክርክር ያለው) የገ ዳሙ መሠረት ፥ በአቅራቢያው የሚገኘው ሜዳና (ኮፕቶች ለመስከቦች የሸጡት) ታች ኛውም የውሀ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ በኮፕቶችና በኢትዮጵያ መነኩሳት መካከል የክ ርክር ምክንያት ሆኖ ቢኖርም ፥ ሡልጣን ገዳም የተባለው (ዴር ኤል ሡልጣን) የኢት ዮጵያ መነኩሳት ንብረት ነው ።

የዛሬ ፵፪ ዓመት የኮፕቶች መነኩሳት በኢትዮጵያውያን እጅ የነበረውን የሡልጣን ገዳም (ዴር ኤል ሡልጣን) መክፈቻ ባልታወቀ ምክንያት ከኢትዮጵያ መነኩሳት ወስ ደው ለኮፕቶች መነኩሳት እንዳስረከቡትና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የገዳሙ ንብረትና ይዞታ መብትነት በኢትዮጵያውያንና በኮፕቶች መነኩሳት መካከል የማያቋርጥ ክርክርና ችግር ፈጥሮ መኖሩንና በዚህም ክርክር ምክንያት በገዳሙ ውስጥ በሚገኙት ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ይፈጸም የነበረው (የኢትዮጵያውያን) ክብረ በዓላትና ሥርዓተ ጸሎታት በኋለኞቹ ዓመታት ተቋርጦ መገኘቱን እናውቃለን ።

አክባሪዎ ነኝ
ፊርማ ፥ በኢየሩሳሌምና ዙሪያዋ
የግሪክ ፓትርያርክ
ማኅተም ፥ ዳሚያኖስ ፤

መስከረም ፯ ቀን ፲፫፻፷፩ ።



አምስተኛው ማስረጃ ።

በእግዚአብሔር ስም በኢየሩሳሌም
የአርመን መንበረ ፓትርያርክ
ቁጥር ፪፻፲፯ ።

ለክቡር ደጃዝማች መሸሻ በይ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ጄኔራል ።

ክቡር ሆይ ፡

በኢየሩሳሌም ውስጥ የሡልጣን ገዳም (ደር ኤል ሡልጣን) በሚል ስም የሚጠራ ሆኖ ከፕቶችና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት የኢትዮጵያ መነኰሳት (አበቶች) ስለሚከራከሩበት የገዳሙ ንብረትነትና ይዘታ መብት ሐሳባችንን በደብዳቤ እንድንገልጽልዎ ክቡርነትዎ ጠይቆናል ።

የኢትዮጵያ መነኰሳት ደር ኤል ሡልጣን (ሡልጣን ገዳም) በሚል ስም በሚጠራው ገዳም ውስጥ ከማናውቀው ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሰፍረው ይኖራሉ ። የገዳሙም መክፈቻ ካለፉት አርባ ዓመታት ወዲህ በከፕቶች መነኰሳት እጅ የቆየ ቢሆንም በምን አኳኋን ወደ እነርሱ እጅ እንደተላለፈ የማናውቀው ነገር ነው ።

ከዚህም ይበልጥ መክፈቻው ወደ ከፕቶች ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የገዳሙ ባለንብረትነትና የይዘታው መብት እንዲታወቅላቸው የኢትዮጵያ መነኰሳት ሳያቋርጡና ሳይሰለቹ የሚከራከሩበት መሆኑንና እስከ አለፉት ጥቂት ዓመታት ድረስም መንፈሳዊ ክብረ በዓላትንና የተለመደ የዘወትር ሥርዓተ ጸሎታትን በክርክሩ ምክንያት ከመፈጸም ያቋረጡ መሆናቸውን ጭምር እናውቃለን ።

የክቡርነትዎ አክባሪ ነኝ
በኢየሩሳሌምና ዙሪያዋ
የአርመን ፓትርያርክ
ማጎቲም ።

መስከረም ፲፬ ቀን ፤ ፲፰፻፸፩ ።

ALOISIUS PICCARDO

MISERATIONE DIVINA ET APOSTOLICÆ SEDIS GRATIA

EPISCOPUS TITULARIS CAPHARNEI

VACANTE SEDE HIEROSOLYMITANA

VICARIUS GENERALIS

ETC.

Io sottoscritto, Vicario Capitolare Amministratore del Patriarcato Latino di Gerusalemme, fondato sulla testimonianza di Anziani della popolazione Latina di questa Città, fo fede e testifico che il Convento degli Abissini, oggetto del conflitto tra questi ed i Copti, è ab antiquo in disposizione e quindi possesso degli Abissini, poichè in esso hanno sempre abitato e fatto le loro preghiere con tutte le loro cerimonie ecclesiastiche.

In fede ecc.

Gerusalemme, dal Patriarchio Latino, li 10 Ottobre ct. del J. 1905

+ Luigi Piccardo
Vic. Gen.mo

ስድስተኛው ማስረጃ ።

አሎኢሲዩስ ፒካርዶ
በእግዚአብሔር ምሕረትና በሐዋርያ ጸጋ
ጳጳስ (ኤጲስቆጶስ) ዘቅፍርናሆም

በኢየሩሳሌም የክፍቱ ወንበር
ጠቅላይ እንደራሴና አስተዳዳሪ ።

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩ በኢየሩሳሌም የላቲን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ እን ደራሴና መልእክተኛ ይኸንን በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ላቲናውያን ሽማግሌዎች ቃል የተመሠረተውን ምስክርነት ስሰጥ፣ ኢትዮጵያውያን በገዳሙ ምክንያት ከክፕቶች ጋር ሲከራከሩ የኖሩ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያውያን ይኸንን ገዳም ከጥንት ዘመን ጀም ሮ ይዘውት የኖሩና ሥርዓተ ጸሎታቸውንና ሌላም ማናቸውንም መንፈሳዊ ሥርዓታት ሲፈጽሙበት የኖሩ መሆናቸውን በዚህ ምስክርነቴ አረጋግጣለሁ ።

በኢየሩሳሌም የላቲን መንበረ ፓትርያርክ
ፊርማ፣ አሎኢሲዩስ ፒካርዶ
ጠቅላይ እንደራሴና አስተዳዳሪ፤
የጽሕፈት ቤቱ ማኅተም ።

ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፫ ።

البطريركية المارونية
بالقدس
PATRIARCAT MARONITE
Jérusalem

Jérusalem le 190

Je soussigné rends témoignage d'après les documents trouvés dans nos archives, que le couvent de Deir El Soultan est propriété des Abyssins; et depuis quinze ans que j'suis à Jérusalem j'ai toujours vu et entendu que le dit couvent de Deir El Soultan et leur propriété et habité par eux, j'ai même assisté a leurs offices religieux dans les deux chapelles qui se trouve dans le passage conduisant de leur couvent de Deir El Soultan au parvis du St Sépulcre

Jérusalem le 24 Août 1905

ዓለቃ ኤል. ፓቭሊ ዓለማ፡
ለሊ. ኤፍ. ሠለማ ማሮ. ንጉሥ ዓ.
ዓለቃው፡ ነጋሥ ዘኢትዮጵያ ማለኢ.
ዓለ. ፲ው. አንቶኒዮስ

Pr El. Mouallem
Chorévêque de Jérusalem
vicaire Patriacal Maronite

JÉRUSALEM


ሰባተኛው ማስረጃ ።

የማሮናይት መንበረ ፓትርያርክ
በኢየሩሳሌም ።

እኔ ከዚህ ግርጌ ላይ የፈረምሁ በኢየሩሳሌም የማሮናይት ጳጳስ በእጃችን በሚገኙት መዛግብት መሠረት እንደሚታወቀው ሁሉ፥ ዴር ኤል ሱልጣን (ሱልጣን ገዳም) የተባለው ገዳም የኢትዮጵያውያን ንብረት መሆኑን እመሰክራለሁ ። በኢየሩሳሌም ከተቀመጥኩባቸው ካለፉት ፲፭ ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የተጠቀሰውን ገዳም የግል ንብረት አድርገው በመያዝ ወትሮም የሚኖሩበት መሆኑን ከመስማቴም ይበልጥ በዓይኔም አይቼ አለሁ ። ከዚህም በላይ መንፈሳዊ ክብረ በዓሎቻቸውን ከዴር ሱልጣን (ሱልጣን ገዳም) ወደ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን ምድረ ግቢ በሚያስገቡት ሁለት ቤተ መቅደሶቻቸው ውስጥ ሲያከብሩና ሥርዓታቸው ቅዳሴም ሲፈጽሙ አብሬ ያከበርኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ ።

ፊርማ ፡ ጄ. ኤል. ሙዓሊም
በኢየሩሳሌም የማሮናይት ጳጳስና
የማሮናይት መንበረ ፓትርያርክ እንደራሴ
የመንበረ ጵጵስናው ማኅተም ።

በነሐሴ ፭፩ ቀን ፲፱፻፭፩ ተሰጠ ።



ስምንተኛው ማስረጃ ።

ለክቡር ደጃዝማች መሸሻ በይ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ጄኔራል ።

ክቡር ሆይ ፣


በኢየሩሳሌም ዴር ሱልጣን ተብሎ በሚጠራው ገዳም ምክንያት በኢትዮጵያና በኮፕት መነከሳት መካከል ስለ ተነሣው የገዳሙ ንብረትነት ክርክር፣ እንዲሁም በገዳሙ ውስጥ ስለሚገኙት ሁለት ቤተ ክርስቲያናትና ስለ በሩ ቍልፍ የምናውቀውን ያክል ማስረጃ እንሰጥዎ ዘንድ የጠየቁበት ጽሑፍ ደርሶናል ።

በእኛ ዘንድ እንደሚታወቀው ሁሉ ዴር ሱልጣን ተብሎ የሚጠራው ገዳም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያውያን እጅ የቆየና በውስጡም መንፈሳዊ ሥርዓቶቻቸውን ሲፈጽሙበት የኖረ መሆኑን ስንገልጽልዎ ፣ የበሩ ቍልፍ ወደ ኮፕቶች የገባበት ዘዴ ፣ ዘመንና ቀን ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን እላይ በተጠቀሱት ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ይፈጽሙዋቸው የነበሩትን ክብረ በዓላትና ሥርዓተ ጸሎታት ሁሉ ያቋረጡበትን ምክንያት ግን የማናውቀው መሆናችንን በዚህ ደብዳቤአችን ለማስረዳት እንወዳለን ።

ይኽ ማስረጃ በሚገባ የተሰጠ ስለ ሆነ የክቡርነትዎን ትእዛዝ ለመቀበል ይጠባበቃል።

የክቡርነትዎ ነኝ
በኢየሩሳሌም የጥንታዊው የሶርያ ገዳም ጳጳስ
ፊርማ ፣ ኤልያስ
ማኅተም ።

ዛሬ መስከረም ፲፬/፲፱፻፲ ዓ. ም.



ARM. CAT. JÉRUSALEM
بطريركية الأرمن الكاثوليك
بالقدس

Je soussigné rends témoignage que depuis les trente cinq ans que je suis à Jérusalem comme vicaire patriarcal, j'ai toujours vu le Couvent St. Deir es Soultan, propriété des Abyssins et habité par des Abyssins, j'ai vu aussi que les Abyssins célébraient toujours leurs offices religieux dans les deux petites chapelles, l'une de St. Michel et l'autre des quarante Martyrs qui sont situées dans le passage par lequel on descend du couvent Deir Es Soultan à l'atrium du Saint Sépulcre Il peut y avoir environ vingt cinq ans de la

Jérusalem. 23 Août 1905 Isachin Kassmayan

Abbé initié, vicaire patr. arménien catholique

ዘጠነኛው ማስረጃ ።

የአርመን ካቶሊካዊ ፓትርያርክ እንደራሴ
በኢየሩሳሌም ።

እኔ እዚሁ ግርጌ የፈረምሁ፣ የፓትርያርክ እንደራሴ ሆኜ ባለፉት ፴፭ ዓመታት በኢየሩሳሌም ውስጥ ስቀመጥ ዴር ሱልጣን የተባለው ገዳም የኢትዮጵያውያን ንብረትና ይዞታ መሆኑን አውቃለሁ ። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን ከዴር ሱልጣን ገዳም ወደ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን ምድረ ግቢ በሚያስገባው መተላለፊያ (ኮሪ ዶር) በሚገኙት ሁለት ትንንሽ ቤተ መቅደሶቻቸው ማለት በቅዱስ ሚካኤልና በአርብዓ ሰማዕታት ፣ ፬ቱ እንስሳ ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ሥርዓቶቻቸውን ሲፈጽሙና ሲያከብሩ ያየሁዋቸው መሆኔን አመሰክራለሁ ።

ሥርዓተ ጸሎቱ ለ፹፭ ዓመት ያህል በዚሁ ዓይነት ተከብሮአል ።

በኢየሩሳሌም የካቶሊካውያን አርመኖች
የፓትርያርክ እንደራሴ
ፌርማ ፣ ዮአቂም ተመያን ።

ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፩ ዓ. ም.